## ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም!!

በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች
የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን መመሪያ

© ትምህርት ሚኒስቴር
2003 ዓ.ም

# በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን መመሪያ

ትምህርት ሚኒስቴር
ነሐሴ 2003

## ማውጫ


| ርዕስ | | ገጽ |
|---|---|---|
| **መግቢያ** | | 1 |
| | የመመሪያው አስፈላጊነት | 2 |
| | የመመሪያው ዓላማ | 3 |
| | የሱፐርቪዥን መርሆዎች | 4 |
| ምዕራፍ አንድ | **የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን አደረጃጀትና የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች** | 7 |
| 1.1 | አደረጃጀት | 7 |
| 1.2 | የአ/መሰ/ት/ሱፐርቪዥን አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች | 9 |
| ምዕራፍ ሁለት | **ለአማ/መሰ/ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የሱፐርቪዥን አገልግሎት ለመስጠት በቅደም ተከተል መከናወን የሚገባቸው** | 13 |
| 2.1 | የቅድመ ሱፐርቪዥን ተግባራት | 13 |
| 2.2 | የክትትል ግምገማና ድጋፍ ተግባራት | 17 |
| 2.3 | የድህረ ሱፐርቪዥን ድጋፍ ተግባራት | 29 |
| ምዕራፍ ሶስት | **ከአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ሱፐርቫይዘሮች የሚጠበቁ ተግባራት" ሥነምግባርና ክህሎት** | 32 |
| 3..1 | የአማ/መሰ/ት/ሱፐርቫይዘሮች ተግባራት | 32 |
| 3.2 | ከአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮች የሚጠበቁ ሥነምግባራት | 36 |
| 3.3 | የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮች ሊኖሯቸው የሚገቡ ክህሎቶች | 37 |







| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ አራት | የባለድርሻዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት | 39 |
| 4.1 | የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር የሥራ ድርሻና ኃላፊነት | 39 |
| 4.2 | የክልል ትምህርት ቢሮ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት | 40 |
| 4.3 | የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የሥራ ድርሻና ኃላፊነት | 43 |
| 4.4 | መንግሥስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት | 45 |
| 4.5 | የቀበሌ ትምህርትና ሥልጠና ቦርድ /የጣቢያ ትምህርት አመራር ኮሜቴ/የሥራ ድርሻና ኃላፊነት | 46 |
| 4.6 | የአመቻቾች የሥራ ኃላፊነት | 47 |
| 4.7 | የመደበኛ ትምህርት ቤቶች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት | 48 |
| 4.8 | የመደበኛ ትምህርት ቤቶች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት | 49 |
| 4.9 | የአማ/መሰ/ትምህርት ተማሪዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት | 50 |
| ምዕራፍ አምስት | **የአማ/መሰ/ት/ሱፐርቪዥን ግምገማ ሪፖርት አቀራረብ** | 51 |
| 5.1 | ሪፖርት አቅራቢዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ጉዳዮች | 52 |
| 5.2 | ሪፖርት መፃፍ ከመጀመሩ በፊት መታወቅ ያለባቸው ጉዳዮች | 53 |
| 5.3 | የሪፖርት ዋና ዋና ክፍሎች | 55 |
| 5.4 | በሪፖርት አጻጻፍ ላይ መሰረታዊ መመሪያዎች | 58 |
| አባሪ | ........................................................................ | 61 |

## መግቢያ

በአገራችን የአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር አካባቢዎች ስር ሰዶ የኖረውን ዝቅተኛ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ችግር በመደበኛው የትምህርት አቅርቦት መንገድ ብቻ ማቃለል እንደማይቻል በመንግስት በኩል ግንዛቤ በመወሰዱ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም ተዘርግቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

ኘሮግራሙ ከአርብቶ አደሩና ከፊል አርሶ አደሩ የኑሮ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ በመቀረፁና አካባቢ ያፈራውን የተማረ የሰው ሀይል የሚጠቀም በመሆኑ የአካባቢዎቹን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ምጣኔና ፍትሀዊ ሥርጭት በአጭር ጊዜ ውስጥ አበረታች በሆነ መጠን እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

ነገር ግን በኘሮግራሙ አተገባበር ዙሪያ የሚታዩ ፈርጀ ብዙ የአፈፃፀምና የግብዓት ችግሮች በሚሰጠው ትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደራቸውን የመስክ ግምገማ ሪፖርቶች ያመለክታሉ፡፡ ስለሆነም በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም የሚሰጠውን ትምህርት ጥራት ደረጃ የሚያስጠብቅ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ በተግባር ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ እንደሚታወቀው በአመቻቾች የትምህርት ደረጃ ዝቅተኝነትና የክህሎት ክፍተት እንዲሁም ከበርካታ የግብዓት ችግሮች አንጻር አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀሩ በርካታ እጥረት የሚታይባቸው ናቸው ፡፡ ስታንዳርዱን ሥራ ላይ ማዋልና የሚገጥሙ ችግሮችን በመፍታት የሚሰጠውን ትምህርት ጥራት ማስጠበቅ እንዲቻል ከመደበኛው የተለየና ወጥ የሆነ የሱፐርቪዥን አገልግሎት ለአማራጥ መሰረታዊ





ትምህርት ፕሮግራም ማዘጋጀት የግድ ይላል፡፡ ስለሆነም ይህ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የሱፐርቪዥን መመሪያ ሲተገበር በቋሚም ሆነ በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ዘንድ መልካም ተሞክሮን በማስፋፋት የትምህርቱን ጥራት ማስጠበቅ ይቻላል ተብሎ ይታመናል፡፡

መመሪያው በአራት ምዕራፎች የተዋቀሩ ይዘቶችን አካትቷል፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን አደረጃጀትና የአገልግሎት መስጫ ዘዴዎች እንዲሁም የሱፐርቪዥን ተግባራትና ቅደም ተከተላዊ አፈጻጸም ተቃኝቷል፡፡ በሶስተኛው ምዕራፍም የሱፐርቫይዘሮች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት እንዲሁም ሊኖራቸው የሚገባ ክሂሎትና ሥነ ምግባር በዝርዝር ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ አራት ደግሞ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን በተጠናከረ የሱፐርቪዥን አገልግሎት ከመደገፍ አኳያ አግባብ ያላቸው ባለድርሻዎች ሊወጡት የሚገባ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ተለይቶ ተቀምጧል፡፡

### የመመሪያው አስፈላጊነት

የአማ/መሰ/ት/ሱፐርቪዥን በትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የሚካሄደውን የማስተማር ሥራ ለማሻሻልና ፕሮግራሙ የታለመለትን ግብ ለማሳካት የሚሰጥ አገልግሎት እንደመሆኑ መጠን በተቀናጀና ወጥ በሆነ መልኩ ሊካሄድ ይገባዋል፡፡ በአንፃሩ በየጊዜው በተካሄደው የመስክ ግምገማ የተገኙ ግብረመልሶች እንደሚያመለክቱት ኘሮግራሙን ለመደገፍ የሚካሄዱ የሱፐርቪዥን ተግባራት የተዘበራረቁ፣ በሱፐርቫይዘሮች ፍላጐት ላይ የተመሠረቱ፣ ተከታታይነት የሌላቸውና በዕቅድ የማይመሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍና አማራጭ መሠረታዊ

ትምህርት ኘሮግራምን በተጠናከረ የሱፐርቪዥን አገልግሎት ለመደገፍ ይቻል ዘንድ ይህን መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጓል። በመሆኑም ክልሎችም ይህንን መመሪያ እንዳስፈላጊነቱ ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመው እንዲያውሉ ይጠበቃል።

**የመመሪያው ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዋነኛ ዓላማ በአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር አካባቢዎች የሚካሄደውን የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም ብቃት ባለው የሱፐርቪዥን አገልግሎት በመደገፍ የሚሰጠውን ትምህርት ጥራት ደረጃ ለማሻሻልና ከመደበኛው ትምህርት ኘሮግራም ተመጣጣኝ የሆነ የትምህርት አገልግሎት እንዲሰጥ የበኩሉን አስተዋፆኦ ማበርከት ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን አገልግሎት አሰጣጥ ኘሮግራሙን በሚያካሂዱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በቅንጅትና ወጥነት ባለው መንገድ እንዲካሄድ ማድረግ፣
- በማዕከል የተዘጋጁት የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ስታንዳርድና የአተገባበር መመሪያዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣
- ተከታታይነት ያለው ሙያዊ ድጋፍ ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አመቻቾች በመስጠት የማስተማር ብቃታቸውን ማሳደግ፣
- በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራር አካላት የኘሮግራሙን አፈፃፀም ከማሻሻል አኳያ በእውቀት ላይ የተመሠረቱ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ማገዝ፣

**የሱፐርቪዥን መርሆዎች**





ትክክለኛውን አቅጣጫ ተከትሎ በተጠናከረና በተባበረ ኃይል የሱፐርቪዥኑን ተግባሮች መፈፀምና ተገቢውንና ትክክለኛውን እርምጃ መውሰድ የሱፐርቪዥን መሰረታዊ ደንብ ነው ፡፡ ይህ መመሪያም መሰረት ያደረገው የሚከተሉትን ሦስት የሱፐርቪዥን መሰረታዊ መርሆዎች ነው፡፡

### ሱፐርቪዥን የኅብረት ሥራ ነው (Cooperative)

ይህ መሰረታዊ መርህ የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቪዥን በተናጠል የሚከናወን ወይም ለሱፐርቫይዘሮች ብቻ የሚተው ሳይሆን በኅብረት የሚከናወን ተግባር መሆኑን ይገልፃል፡፡ የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቪዥን በክላስተር ወይም በወረዳ ሱፐርቫይዘሮች ብቻ የሚከናወን ሳይሆን ከሁለት በላይ አመቻቾች ባሉባቸው ጣቢያዎች በጣቢያ ደረጃ በተጠሪ አመቻቾች አማካይነት" በወረዳ ት/ጽ/ቤት ደረጃ ደግሞ በጽ/ቤት ኃላፊዎች"ሱፐርቫይዘሮች"በክልልና በማዕከል ደረጃ በሚመለከታቸው የትምህርት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ይከናወናል፡፡

በመሆኑም የሱፐርቪዥኑ ሥራ ውጤታማ እንዲሆን ከላይ የተጠቀሱትና ሥራው የሚመለከታቸው ሁሉ በንቃት በመሳተፍ የድርሻቸውን መፈፀም ይኖርባቸዋል ፡፡ የአንዱ ባለድርሻ አካል አፈፃፀም የሌላውን ሥራ ሊያቀላጥፍ ወይም ሊጎትትና ሊያደናቅፍ ስለሚችል ሁሉም ባለድርሻዎች ኃላፊነታቸውን ተገንዝበው በአንድ ዓላማ ለአንድ ውጤት በቅንጅት መስራት የሱፐርቪዥን መርህ ነው ፡፡

**ሱፐርቪዥን የፈጠራ ችሎታን ይጠይቃል (Creativity)**

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የአርብቶ አደሩንና ከፊል አርሶ አደሩን ኅብረተሰብ ወቅታዊ አኗኗርና የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ተከትሎ የሚያድግ" የሚለወጥና የሚሻሻል በመሆኑ የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቪዥንም እንደዚያው የሚሻሻልና የሚለወጥ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮችም ሁልጊዜ ራሳቸውን የሚያሻሻሉና የፈጠራ ችሎታና ዘዴ ያላቸው ሆነው አመቻቾችንም የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያወጡና እንዲጠቀሙ የሚያበረታቱና በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ አሰራርን የሚያዳብሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ይህ በሌላ መልኩ ሲታይ ቀድሞ ያልነበረ አዲስ ዘዴና የአሰራር መንገድ ማስገኘትና በሥራ ላይ ማዋል ወይም የነበረውን በማሻሻል የበለጠ ጥቅምና አገልግሎት እንዲሰጥ የማድረግ ችሎታን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአማ/መሰ/ት/ሱፐርቫይዘሮች የሚሰሩባቸውን ዘዴዎችና የአሰራር መንገዶች በይበልጥ በማሻሻል ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ሊተገበሩ የሚችሉ አዳዲስ ዘዴዎችንም የመፍጠርና የማፍለቅ ችሎታዎች እንዲኖሯቸው አስፈላጊ መሆኑን ነው ፡፡

**ሱፐርቪዥን ቀና አመለካከትን ይጠይቃል (Positive attitude)**





በዚህ መሰረታዊ መርህ የሥራ ውጤት ሊለካና ሊታወቅ የሚችለው በአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮችና ሌሎች በሂደቱ ተሳታፊ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ጤናማና ቀና አስተሳሰብ ሲኖራቸው ነው ፡፡ ቀና አስተሳሰብ ሲባል ማናቸውንም ነገር አሜን ብሎ መቀበል ሳይሆን ኃላፊነትን መውሰድ" ግዴታን መወጣት "ለፕሮግራሙ ቀና አመለካከት ማሳደር" በቀላሉ ተስፋ አለመቁረጥና ችግርን ለመፍታት ያላሰለሰ ጥረት ማደረግ ማለት ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮች ራሳቸው ጤናማ አስተሳሰብ ኖሯቸው በሚያከናውኗቸው ተግባራት ሁሉ መልካም አርዓያ ሆነው ሌሎችም እነርሱን ተከትለው መስራት የሚያስችላቸው ሁኔታ መፍጠር እንዳለባቸው ነው ፡፡

ቀና አስተሳሰብና ሙሉ የመስራት ፍላጎት ያለው ሰው ችግርም ቢያጋጥመው ሞራሉንና መንፈሱን በማጠንከርና በመስራት ከፍተኛ ውጤት ሊያስገኝ ሲችል ቀና አስተሳሰብ የሌለውና መንፈስ ደካማ የሆነው ደግሞ በሥራው ውጤት ሊያገኝ እንደማይችል የተለያዩ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ስለዚህ እንደ አጠቃላይ መርህ የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቪዥን አገልግሎት አሰጣጥ ቀና አመለካከትን ይጠይቃል፡፡



## የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን አደረጃጀትና

# የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች

## 1.1 አደረጃጀት

በመሠረቱ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓታችን አንድ አካል እንደመሆኑ መጠን ለፕሮግራሙ የሚሰጥ የሱፐርቪዥን አገልግሎት የተለየ አደረጃጀት አያስፈልገውም፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ባለው የትምህርት መዋቅር በተቋቋሙ የሱፐርቪዥን ክፍሎች አማካኝነት የሱፐርቪዥን አገልግሎቱን መስጠት ይቻላል፡፡ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ግን የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

### ሀ. የተጠናከረ የሱፐርቪዥን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አቅም መፍጠር

የአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር አካባቢዎች የትምህርት ሱፐርቪዥን ሥርዓት የሚገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ብቻ ሳይሆን ለመደበኛ ት/ቤቶች በቂ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል አይደለም፡፡ ስለሆነም ስርዓቱ ለሁለቱም የትምህርት ፕሮግራሞች ውጤታማና ብቃት ያለው የሱፐርቪዥን አገልግሎት ለመስጠት ይችል ዘንድ የአማራጭና መደበኛ ት/ቤቶችን ብዛትና ስርጭት (ርቀት)፣ የአማራጭ መሠ/ትም/አመቻቾችን ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃና አነስተኛ የቅድመ ሥራ ሥልጠና እንዲሁም የተንቀሳቃሽ አማ/መሠ/ትም/ጣቢያዎችን ልዩ ባሕሪይ





ባገናዘበ ሁኔታ በየደረጃው በተለይም በወረዳ፣ በክላስተርና ማዕከል ደረጃ አስፈላጊውን ስልጠና በወሰደ ባለሙያ፣ በጀትና ሎጂስቲክስ ሊደራጅ ይገባቸል፡፡ በጣቢያ ደረጃ ደግሞ ለአመቻቾች በሱፐርቪዥን አገልግሎት ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### ለ. ሱፐርቫይዘሮች በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

በየደረጃው የሚገኙ ሱፐርቫይዘሮች ከመደበኛ ት/ቤቶች ጎን ለጎን ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችም በእውቀት ላይ የተመሠረተና ውጤታማ የሱፐርቪዥን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የአማራጭ መሠ/ትም/ ኘሮግራምን ምንነት፣ ስታንዳርድና የአተገባበር መመሪያዎች ጠንቅቀው እንዲያውቁ ማድረግ የማይታለፍ ተግባር ነው፡፡

## 1.2 የአ/መሰ/ት/ሱፐርቪዥን አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች

የአማ/መሰ/ት/ሱፐርቪዥን አገልግሎት የሚከተሉትን ሶስት መንገዶች በማቀናጀት ይካሄዳል፡፡

### 1.2.1. ውጫዊ የሱፐርቪዥን አገልግሎት (External Supervision)

- ይህ የሱፐርቪዥን አገልግሎት የሚሰጠው ከትምርት መስጫ

ጣቢያው ውጪ (ከክላስተር ማዕከል፣ ከወረዳ፣ ከክልል) በሚመጡ ሱፐርቫይዘሮች ወይም የትምህርት ባለሙያዎች አማካይነት ነው። የሚሰጠው ድጋፍም የሚያተኩረው#

- የትምህርት ፕሮግራሙ ከአካባቢው ሁኔታና ከህብረተሰቡ ፍላጐት ጋር ተጣጥሞ መሰጠቱን ማረጋገጥ፣
- ለትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በሚፈለገው መጠንና ዓይነት መቅረባቸውንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን፣
- ፕሮግራሙን ውጤታማ ለማድረግ የተዘጋጁ መመሪያዎች፣የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ስታንዳርድና ሌሎች መሰል ሰነዶች በሚፈለገው ዓይነትና መጠን መኖራቸውንና ሥራ ላይ መዋላቸውን ፣
- የመማር ማስተማሩ ሂደት በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ስታንዳርድ ላይ በተቀመጠው የትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት መሰረት ሳይስተጓጐል መካሄዱን፣ … ወዘተ በመከታተልና ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ላይ ያተኩራል።

ውጫዊ የሱፐርቪዥን አገልግሎት በዋናነት በወረዳና በክላስተር ሱፐርቫይዘሮች የሚሰጥ የሱፐርቫይዘሮች እጥረት ካጋጠመም ልምዱ





ያላቸውን ሌሎች ባለሙያዎችን በማሳተፍ የሚሰጥ ሲሆን በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ቋሚና ተንቀሳቃሽ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በሙሉ ይሸፍናል። አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ይሆናል።

- ከመደበኛ መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ጋር በክላስተር የተደራጁ አማራጭ መሠ/ትም/ጣቢያዎችን በተመለከተ ለክላስተር ማእከሉ የተመደበው ሱፐርቫይዘሮች ቢያንስ በየ15 ቀኑ በእያንዳንዱ ጣቢያ በመገኘት የሱፐርቪዥን አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል።
- በርቀት ወይም በተንቀሳቃሽ ባሕሪያቸው ምክንያት በክላስተር ሊደራጁ የማይችሉ ቋሚና ተንቀሳቃሽ የትምህርት ጣቢያዎችን በተመለከተ እያንዳንዱ ጣቢያ ቢያንስ በየወሩ የሱፐርቪዥን ድጋፍ በወረዳው ትም/ጽ/ቤት ሱፐርቫይዘሮች አማካኝነት እንዲያገኙ ይደረጋል።
- በተከናወኑ የመጀመሪያ ዙር የሱፐርቪዥን ተግባራት በተገኘ ግብረመልስ መሰረት የተለየ ችግር ያለባቸው ጣቢያዎችን ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር እስኪስተካከሉ ድረስ ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው በበለጠ የድግግሞሽ መጠን የሱፐርቪዥን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።
- በማዕከልና በክልል ሱፐርቫይዘሮች የሚሰጠው ውጫዊ የሱፐርቪዥን አገልግሎት በየሴሚስተሩ አጋማሽ (በዓመት አራት ጊዜ) በናሙናነት በተመረጡ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ትምህርት

መስጫ ጣቢያዎች ይካሄዳል።

### 1.2.2. በመደበኛ ት/ቤቶችና በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች መካከል የሚካሄድ የሱፐርቪዥን አገልግሎት (Inter-School Supervision)

ይህ ሁለተኛው ዓይነት የሱፐርቪዥን አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴ ሲሆን የድጋፍ አሰጣጡም ከመደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ጋር በአንድ የጉድኝት ማእከል (Cluster Centre) ሥር የተደራጁ የአማራጭ መሠረታዊ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ልምድ የሚለዋወጡበት፣ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችን በጋራ የሚወስዱበት፣ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በአሰራር ሂደት የገጠሚቸውን ችግሮች በጋራ ተወያይተው የሚፈቱበት፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመዋዋስ በጋራ የሚጠቀሙበት፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በጋራ አዘጋጅተው በጋራ የሚጠቀሙበት፣ ከአዳዲስ የመማር ማስተማር ዘዴዎችና አሰራሮች ጋር የሚተዋወቁበትና እርስ በርስ የሚደጋገፉበት የድጋፍ ዘዴ ነው።

### 1.2.3. በትምህርት መስጫ ጣቢያ ደረጃ የሚካሄድ የሱፐርቪዥን አገልግሎት (Inbuilt Supervision)





የዚህ ዓይነት የሱፐርቪዥን ድጋፍ የሚካሄደው በአንድ የትምህርት መስጫ ጣቢያ ውስጥ በሚገኙ አመቻቾች መካከል (በተጠሪ አመቻችና በሌሎች አመቻቾች መካከል) ሲሆን የአገልግሎት አሰጣጡ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ሁለትና ከዚያ በላይ አመቻቾች ባሉበት የትምህርት መስጫ ጣቢያ ነው። ይህ የድጋፍ አሰጣጥ ስልት አመቻቾች በሚያስተምሩበት የትምህርት መስጫ ጣቢያ እርስበርሳቸው ልምድ የሚለዋወጡበት፣ የሥራ አፈፃፀማቸውን በጋራ የሚገመግሙበት፣ ችግሮቻቸውን በጋራ ተወያይተው የሚፈቱበትና እርስበርሳቸው የክፍል ምልከታ በማካሄድ ሙያቸውን ለማሳደግና አሰራራቸውን ለማሻሻል የሚደጋገፉበት ነው።

## ምዕራፍ ሁለት

## ለአማ/መሰ/ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የሱፐርቪዥን አገልግሎት ለመስጠት በቅደም ተከተል መከናወን የሚገባቸው ተግባራትና የአፈፃፀም ሥርዓቱ

### 2.1 የቅድመ ሱፐርቪዥን ተግባራት

በሱፐርቪዥን የሙያ ድጋፍ ለመስጠት የሚሰማሩ ባለሙያዎች ውጤታማ ሥራ ለመስራት በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከሚደረጉት ቅድመ ዝግጅት ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.1.1. አመቻቾች፣ ተጠሪ አመቻቾችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የሚሳተፉበት ድጋፍና ግምገማ ለማድረግ ማቀድ

በግምገማውና ድጋፍ አሰጣጡ ሂደት አመቻቾች፣ ተጠሪ አመቻቾችና የህብረተሰቡ ተወካዮች ቢሳተፉ የትምህርት መስጫ ጣቢያውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በሚገባ እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል። እንዲሁም የትምህርት መስጫ ጣቢያው ያሉበትን ችግሮች ለመፍታት ለሚያዘጋጀው ዕቅድ ማስፈፀሚያ ከሚያስፈልገው የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ውስጥ የህብረተሰቡን ድርሻ በቀላሉ ለማግኘት ያስችለዋል። በመሆኑም ሱፐርቫይዘሮች የእነዚህ ባለድርሻ አካላት የተሳትፎ ደረጃን ለማሳደግ እንዴትና በምን ደረጃና ሁኔታ መሳተፍ እንደሚገባቸው በጥንቃቄ ማቀድ ይኖርባቸዋል።

### 2.1.2. የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን እንደመደበኛው ትምህርት በዓላማ ላይ ተመስርቶ በዕቅድ እየተመራ የሚፈፀም የሥራ ክንውን ነው:: ስለሆነም ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ ላይ የተገለፁ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ የሱፐርቪዥን አገልግሎት ዕቅድ ማዘጋጀት የግድ ነው:: ዕቅዱ በማን እንደሚከናወን፣ ለየትኞቹ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች፣ መቼ እንደሚከናወን፣ የሱፐርቪዥን ድጋፍ እንደሚሰጥ፣ ምን ምን ተግባራት እንደሚከናወኑና ምን ያህል ወጭ እንደሚያስፈልግ፣ የመሳሰሉትን የሚያሳይ





ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብርን ሊያካትት ይገባል::

### 2.1.3. ለቅድመ ዝግጅት የሚረዱ መረጃዎችን ለትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በቅድሚያ ማሳወቅ

የሱፐርቪዥን ድጋፍ ሥራው መቼ እንደሚካሄድ፣ በምን በምን ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩር፣ የሱፐርቪዥን ድጋፍ የሚሰጡ ባለሙያዎች ከትምህርት መስጫ ጣቢያው ምን ምን መረጃዎችን እንደሚፈልጉ፣ በድጋፍ አሰጣጡ የሚሳተፉ የትምህርት መስጫ ጣቢያው አባላት እነማን እንደሆኑ (አመቻቾች፣ ተጠሪ አመቻቾች፣ ጣቢያውን የሚያስተዳደሩ የማህበረሰቡ ተወካዮች፣… ወዘተ)፣ ለትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በቅድሚያ ሊገለጽላቸው ይገባል። ይህ አሰራር ሱፐርቫይዘሮች በቦታው ከተገኙ በኋላ ሊፈጠር የሚችለውን ግራ መጋባት ለመቀነስና ተፈላጊ መረጃዎችን በቀላሉና በአጭር ጊዜ ለማግኘት ከመርዳቱም በተጨማሪ በመግባባት ላይ የተመሰረተ ውጤታማ የሱፐርቪዥን አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል።

### 2.1.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጾችን ማዘጋጀት

የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጾች

- ያልተወሳሰቡ ግልጽና አጭር፣
- ሁሉም ሰው በቀላሉ የሚረዳቸው፣

- ወጥነት ያላቸው ሆነው መዘጋጀት አለባቸው።

ቅጾቹ በየጊዜው የሚለዋወጡ እንዳይሆኑ ሱፐርቫይዘሮች ቅጾችን በሚያዘጋጁበት ጊዜ አመቻቾችና ተጠሪ አመቻቾችን በማወያየትና በማስተቸት እንዲሁም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ስታንዳርድ፣የተንቀሳቃሽና ቋሚ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የአተገባበር መመሪያዎችና ሌሎች መሰል የሥራ ሰነዶችን ባገናዘበ መልኩ በጥንቃቄ ሊዘጋጁ ይገባል። ለዝግጅቱም ከዚህ መመሪያ ጋር በናሙናነት አባሪ የተደረገውን የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቪዥን ቼክ ሊስት ወስዶ አካባቢያዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

የሱፐርቪዥን አገልግሎት የሚሰጥበትን ጊዜ በቅድሚያ እንዲያውቁትና አስተያየት እንዲሰጡበት ከተደረገ ከመማር ማስተማሩ ጎን ለጎን በመግባባት ላይ የተመሰረተ የሱፐርቪዥን አገልግሎት መስጠት ይቻላል።

### 2.1.5. የሱፐርቪዥን ድጋፍ የሚሰጣቸው የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ሁኔታ በተመለከተ በቂ መረጃ መያዝ፣

ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት ወደ ተቋማቱ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ድጋፍ ስለሚሰጧቸው የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የትምህርት መስጫ ጊዜ፣ የአመቻቾች የትምህርት ደረጃና የሥልጠና ሁኔታ፣ የጣቢያ አደረጃጀትና የግብአት ሁኔታ፣ የጣቢያውን ደረጃና የመሳሰሉትን መረጃዎች መያዝ





ይኖርባቸዋል። እነዚህን መረጃዎች ከመዛግብት፣ ቀደም ሲል ከቀረቡ ሪፖርቶችና ሌሎች የመረጃ ምንጮች ማጠናቀር ይገባል።

### 2.1.6. የሱፐርቪዥኑን ሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴ መምረጥ

የሱፐርቪዥን ድጋፍ ለመስጠት ሲታቀድ ከዚህ ጎን ለጎን የሪፖርቱ ይዘት ምን ምን ጉዳዮችን ማካተት አለበት? አዘገጃጀቱ እንዴት ይሁን? የሪፖርት ማቅረቢያዉ ፎርማትስ ምን መምሰል አለበት?... ወዘተ ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ያስፈልጋል።

## 2.2. የክትትል ግምገማና ድጋፍ ተግባራት

የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም በመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም የመማር ዕድል ላላገኙ ህፃናትና ወጣቶች የሚሰጥ የትምህርት አገልግሎት ነው። ትምህርቱ እየተሰጠ ያለው በቂ የትምህርት ዝግጅትና የተሟላ ስልጠና በሌላቸው አመቻቾች ሲሆን የትምህርቱ ፕሮግራም አደረጃጀትም ከመደበኛው አደረጃጀት በተወሰነ መልኩ ለየት ይላል። በሌላ በኩል በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የሚሰጠው ትምህርት በመደበኛው ፕሮግራም ከሚሰጠው ትምህርት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ይጠበቃል። ስለዚህ ፕሮግራሙ ያለበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በመፍታት ተማሪዎች በመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ከሚሰጠው ትምህርት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ በትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል

ውጭ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሥራ በተጠናከረና ተከታታይነት ባለው የሱፐርቪዥን አገልግሎት መደገፍ ይኖርበታል።

የግምገማና ድጋፍ ተግባራት ሱፐርቫይዘሮች በትምህርት መስጫዎች በአካል በመገኘት የጣቢያዎቹንና የትምህርት ፕሮግራሙን አደረጃጀት እንዲሁም የመማር-ማስተማሩን ሂደት በመገምገም ጠንካራ ጎኖችን ለማጎልበትና ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችል ሙያዊ ድጋፍ የመስጠት ሥራዎች ያካትታሉ። እነዚህ ተግባራት የክፍል ውጪና የክፍል ውስጥ በሚል ተከፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 2.2.1 የክፍል ውጪ የሱፐርቪዥን ድጋፍ ተግባራት

እነዚህ ተግባራት ከመማር ማስተማር ውጭ ባሉት የትምህርት መስጫ ጣቢያ ጉዳዩች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ስለሆነም የሱፐርባይዘሮች ተቀዳሚ ተግባር ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አበይትና ንዑሳን ጉዳዩች ላይ ተገቢውን ምልከታና ግምገማ በማድረግ ጠንካራ ጎኖችንና ክፍተቶችን መለየት ነው።

### ሀ) የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች አጠቃላይ ሁኔታ አደረጃጀት

የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ስታንዳርድ ላይ በተቀመጠው መሠረት፡-

- ቋሚ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በቂ ምድረግቢ፣ አጥር፣ በአስፈላጊ ቁሳቁሶች የተደራጁ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች፣ የመጫወቻ ሜዳ፣ለወንዶችና ለሴቶች የተለያዩ መፀዳጃ ቤቶች፣





የመጠጥ ውሃና የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና አገልግሎቶች ወዘተ ያሏቸው ስለመሆኑ፣

- ተንቀሳቃሽ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ከቦታ ቦታ በቀላሉ ሊጓጓዙና ከአካባቢው አየር ንብረት ጋር ተስማሚ የሆኑ ድንኳኖች፣ የዳስ መጠለያዎች፣ የትምህርት ቁሳቁሶች(Furnitures)" የትምህርት መሳሪያዎች (Teaching Materials) እና የተለያዩ ዶኩሜንቶች ማስቀመጫ የሸራ ሻንጣዎች ወይም ቀላል ሳጥኖች፣ ጊዜያዊ መፀዳጅ ቤቶች፣ የመጠጥ ውሀና የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና አገልግሎቶች ያላቸው ስለመሆኑ፣
- የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ "የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ"የአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር አካባቢዎች የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ስታንዳርድ"የቋሚና ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አተገባበር ማንዋሎች"የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አመቻቾች ማሰልጠኛ ማንዋል" የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የየትምህርት ዓይነቱ መርሃ ትምህርትና ሌሎች መመሪያዎችና ደንቦች በትክክል ሥራ ላይ ስለመዋላቸውንና በትምህርት መስጫ ጣቢያው የሚሰጠው ትምህርት ስታንዳርዱ የተጠበቀ ስለመሆኑ"
- ሳምንታዊ የትምህርት ቀናት ብዛትና አወሳሰን እንዲሁም የየደረጃውና

የየትምህርት ዓይነቱ የክፍለ ጊዜ ስርጭት በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ስታንዳርድ መሠረት ስለመፈፀሙ

- በየትምህርት መስጫ ጣቢያው የተመደቡ አመቻቾች ብዛት ከጣቢያው ተማሪዎች ብዛት ጋር የተመጣጠነ ስለመሆኑ፣
- የየደረጃውና የየትምህርት ዓይነቱ የመማሪያ ማስተማሪያ መፃህፍት በበቂ መጠንና በወቅቱ ለጣቢያው ስለመድረሳቸውና የመማሪያ መፃሕፍቱ ለተማሪዎች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ስለመሰራጨታቸው እንዲሁም በየትምህርት ዓይነቱ በቂ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ስለመኖራቸው

## ለ) የፋይል አደረጃጀትና የትምህርት መረጃ አያያዝ

- የተማሪዎች ባሕረመዝገብ፣ የቃለ ጉባኤ መዝገብ፣ የንብረት መዝገብ፣ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ፋይሎች፣ ቢያንስ በወረዳ ደረጃ ወጥነት ባለው መልክ የተዘጋጁ የተማሪዎች ሥም መጥሪያ (አቴንዳስ)፣ የተከታታይ ምዘና ወጤት መመዝገቢያ ቅጾች፣ የውጤት ማጠናቀሪያና ማጠቃለያ/ሮስተር/፣ ወዘተ በትምህርት መስጫ ጣቢያዎች፣ ስለመኖራቸው እና ሥራ ላይ ስለመዋላቸው እና በአግባቡ ፋይል ተደርገው ስለመያዛቸው፤
- የትምህርት ዘመኑ የትምህርት መረጃዎች ማለትም፣





- ◊ የተማሪዎች መረጃዎች (በዓመቱ መጀመሪያ የተመዘገቡ፣ ያቋረጡ፣ ለፈተና የተቀመጡ፣ ያለፉ/የደገሙ፣ወዘተ ተማሪዎች ብዛት በደረጃና በፆታ)
- ◊ የአመቻቾች መረጃዎች (ሥም ዝርዝር፣ ፆታ፣ የትምህርት ደረጃ የአገልግሎት ዘመን ወዘተ)
- ◊ የጣቢያ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃዎች (የምድረገ ግቢ ስፋት፣የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችና የትምህርት ቁሳቁሶች ዓይነትና ብዛት፣ትምህርት የሚሰጥባቸው ደረጃዎች በጣቢያው ውስጥ ያሉ አገልግሎቶች፣ ወዘተ) ተጠናቅረው ስለመያዛቸው፣

- የጣቢያውን ወቅታዊ (የትምህርት ዘመኑን)የትምህርት እንቅስቃሴ የሚያሳዩ መረጃዎች (የተማሪዎችና የአመቻቾች መረጃዎች፣ ዓመታዊ እና ሳምንታዊ የትምህርት ዕቅድ፣ ሳምንታዊ የትምህርት ክ/ጊዜ ሰሌዳ፣ የትምህርት ኮሚቴ አባላት ሥም ዝርዝር፣ወዘተ) በቀላሉ ሊታዩ በሚችሉበት መልክ በቻርት ተዘጋጅተው በአመቻቾች ቢሮ ስለመለጠፋቸው፣

## ሐ) የትምህርት አመራርና አስተዳደር

- የጣቢያ ትምህርት አመራር ኮሚቴ በመመሪያው መሰረት ስለመቋቋሙ፣

- ኮሚቴው መደበኛ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ደንብ ያለው ስለመሆኑ፣ የእያንዳንዱ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ስለመያዙ፣ የጣቢያውን የትምህርት እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜትና በትጋት ስለመምራቱ
- የትምህርት ብክነትን በተለይም መጠነ ማቋረጥን ለመቀነስ እንዲሁም የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎና ዘለቄታ ለማሳደግ የተለያዩ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ ስለመደረጋቸውና ውጤት ስለማስገኘታቸው፣
- የጣቢያው ንብረትና ገንዘብ በአግባቡ ስለመያዙና ጥቅም ላይ ስለመዋሉ
- የት/ቤቶች ድጎማ በጀት (School grant) ገንዘብ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ባለድርሻዎችን ባሳተፈ መልኩ እቅድ ተዘጋጅቶለት ሥራ ላይ ስለመዋሉና ሂሳቡ በወቅቱ ስለመወራረዱ፣
- አመቻቾች ተገቢ የሆነ የትምህርት ዕቅድ በማዘጋጀትና የሥራ ዲሲፕሊንን በማክበር ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማድረግ የክትትል የድጋፍና ቁጥጥር ሥርዓት ስለመኖሩ፣
- የተማሪዎች ምዘና፣የትምህርት ማስረጃ አሰጣጥና የደረጃ ሽግግር በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ስታንዳርድ መሠረት ስለመፈፀሙ፣

### መ) ዓመታዊ ዕቅድ ዝግጅት አፈፃፀምና ሪፖርት

- የጣቢያው ዓመታዊ እቅድ ባለድርሻዎችን በማሳተፍ ስለመዘጋጀቱ





- ዕቅዱ በተነደፈለት የትግበራ መርሃግብር መሠረት ስለመከናወኑ
- ወርሃዊ የእቅድ ክንውን ግምገማ ስለመካሄዱና የአፈፃፀም ሪፖርት ለወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት በወቅቱ ስለመላኩ፣

### ሠ) የህብረተሰብ ተሳትፎ

- በትምህርት መስጫ ጣቢያና በወላጆች (ሕብረተሰብ) መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖርና ሕብረተሰቡ የትምህርቱን ሥራ በገንዘቡ፣ በእውቀቱና በጉልበቱ እንዲደግፍ የተደረገ ጥረትና የተገኘ ተጨባጭ ውጤት ስለመኖሩ፤
- የሱፐርቫይዘሮች ቀጣዩ ተግባር በምልከታና ግምገማ የተሰባሰቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ በአንድ በኩል ጠንካራ ጎኖች ይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ማበረታታት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የታዩ ክፍተቶችን መሙላት ይቻል ዘንድ እንደ ክፍተቶቹ ዓይነትና ደረጃ አስፈላጊውን የሱፐርቪዥን ድጋፍ መስጠት ነው። ስለሆነም ሱፐርቫይዘሮች፤
    - ◊ በጣቢያ ደረጃ ሊሟሉ የሚገባቸውን የግብአት ክፍተቶች በተመለከተ ከጣቢያ ትምህርት አመራር ኮሚቴ ጋር በመወያየት ክፍተቶች በተወሰነ የጊዜ ገደብ በተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚሟሉበትን አቅጣጫ በማስቀመጥ፣

◊ በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃና በክልል ትምህርት ቢሮ ደረጃ ሊሟሉ የሚገባቸው የግብዓት ክፍተቶች ካሉም በሱፐርቪዥን ሪፖርታቸው ውስጥ አካትተው ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ክፍተቶቹ እንዲሟሉ አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ

◊ ከስታንዳርዱና ከመመሪያ ውጭ የሆኑና የተሳሳቱ አሰራሮች እንዲታረሙ፣ ያልተጀመሩ ሥራዎች እንዲጀመሩ ጅምር ጥረቶች እንዲጠናከሩ ከማድረግ አኳያ ተገቢውን ግንዛቤ በማስጨበጥ፣ እንዳስፈላጊነቱ በተግባር የተደገፈ ሙያዊ ድጋፍ በመስጠትና መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር ከጣቢያ-ጣቢያ በማስፋፋት ኃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

## 2.2.2. የክፍል ውስጥ የሱፐርቪዥን ድጋፍ ተግባራት

- የክፍል ውስጥ የሱፐርቪዥን ድጋፍ ተግባራት ሱፐርቫይዘሮች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በአካል ተገኝተው በመማር ማስተማሩ ሂደት ልዩ ልዩ ገጽታዎች ላይ ምልከታ በማድረግ ክፍተቶችን በመለየት መማር ማስተማርን ለማሻሻል የሚሰጧቸውን ሙያዊ እገዛዎችን ያካትታሉ።
- ሱፐርቫይዘሮች ለምልከታ ክፍል ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ቀደም ብለው በያዙት ቀጠሮ መሰረት ተገኝተው የአመቻቾችን ፈቃድ





በመጠየቅ አክብሮታቸውን ማሳየት፣ ክፍል ውስጥ ከገቡ በኋላ የተማሪዎች ትኩረት ወደ እነርሱ እንዳይሳብና የመማር-ማስተማሩ ሂደት እንዳይታወክ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በክፍል ውስጥ ምልከታ ሱፐርቫይዘሮች ትኩረት ሊሰጧቸው የሚገቡ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው።

### ሀ) የመማሪያ ክፍል አጠቃላይ ሁኔታን /ድባብን/በተመለከተ

- የክፍሉ ጽዳት፣ የተማሪ ዴስክ ጥምርታና የተማሪዎች አቀማመጥ፣
- ትምህርት ነክና ቀስቃሽ የሆኑ የጽሑፍና የስዕል ፖስተሮችን ክፍል ውስጥ በመለጠፍ ምቹ የትምህርት ድባብ ለመፍጠር የተደረገ ጥረት፣
- በክፍል ውስጥ በቂ ብርሃንና አየር ስለመኖሩ፣

### ለ) አመቻቾችን በተመለከተ

- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድና ተገቢ የትምህርት መሣሪያዎችን ይዘው ክፍል ስለመግባታቸው፣
- በእቅዳቸው መሠረት ስለማስተማራቸውና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ ስለመጠቀማቸው፣
- የተማሪዎቻቸውን ትኩረት የመሳብና ዲሲፕሊን የማስጠበቅ

ብቃታቸው፣

- ተማሪዎቻቸውን በትምህርት አቀባበል ችሎታቸው መለየትና የትምህርት አቀራረባቸው ይህን ልዩነት እንዲያስተናግድ ለማድረግ ያደረጉት ጥረት፣
- ተማሪ-ተኮር የማስተማር ሥነዘዴን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የተጓዙት ርቀት በተለይም በማስተማር-መማሩ ሂደት የሴቶችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መጎልበት የሰጡት ትኩረት፣
- የክ/ጊዜውን ትምህርት የጀመሩበትና የጨረሱበት ሁኔታ/ስለአለፈው ክ/ጊዜ ትምህርት አንኳር ጭብጦች በማስታወስና የዕለቱን ክ/ጊዜ ትምህርት በማስተዋወቅ ስለመጀመራቸው፣ በክ/ጊዜው መጨረሻም ማጠቃለያ ስለመስጠታቸው፣
- አንድን የትምህርት ርዕስ ጨርሰው ወደ ሚቀጥለው ከመሸጋገራቸው በፊት ተማሪዎች የተሰጠውን ትምህርት መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ የግምገማ ዘዴዎችን ስለመጠቀማቸውና የግምገማውን ግብረመልስ መሠረት በማድረግ ቀጣይ እርምጃቸውን ስለመወሰናቸው፣
- በየትምህርት ዓይነቱ የደረሱበት ምዕራፍ በዓመታዊ የትምህርት እቅድ ከተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ጋር ስለመጣጣሙ፣
- ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ፡-





◊ ለተማሪዎቻቸው በቂ የክፍልና የቤት ሥራዎችን እንዲሁም ሙከራዎችን ስለመስጠታቸው፣

◊ አርመው ውጤት ለተማሪዎች ስለማሳወቃቸውና በውጤት ማጠራቀሚያ ቅጽ በአግባቡ መዝግበው ስለመያዛቸው (የተማሪዎችን ደብተርና የተማሪ ውጤት ማጠራቀሚያ ቅጽ በመመልከት)፣

- የምዘና ውጤቶችን መሠረት በማድረግ ለተማሪዎቻቸው ድጋፍ ለመስጠታቸው ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ፡-

◊ ለተማሪዎቻቸው ቅርብና ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል ዓይን /ያለአድልዎ/የሚያዩ ስለመሆናቸው፣

◊ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ለማበረታታት፣ ትምህርት-ነክ እና ከትምህርት ውጭ የሆኑ ችግሮቻቸውን ለማድመጥና አቅም በፈቀደ መጠን ለማቃለል ጥረት ስለማድረጋቸው፣

**ሐ) ተማሪዎችን በተመለከተ**

- በክፍሉ የተመደቡ ተማሪዎች ብዛት በፆታ፣
- በምልከታ ወቅት ክፍል ውስጥ የተገኙ ተማሪዎች ብዛት በፆታ፣

- ተማሪዎች መማሪያ መፃህፍትና አስፈላጊ የጽህፈት መሳሪያዎች ይዘው ስለመገኘታቸውና በንጽህና ስለመያዛቸው፣
- የተማሪዎች የግል ንጽህና አጠባበቅ፣
- ተማሪዎች በሚሰጠው ትምህርት ላይ ያላቸው አትኩሮትና ጥያቄ በመጠየቅ ለጥያቄ መልስ በመስጠት ወዘተ በመማር ማስተማሩ ሂደት ያላቸው ንቁ ተሳትፎ፣
- የተማሪዎች ሥነ ሥርዓት አጠባበቅ፣
- የተማሪ-ተማሪ ግንኙነት፣ (እርስ በእርስ መረዳዳት፣በቡድን መስራት ወዘተ)፤

## 2.3 የድህረ ሱፐርቪዥን ድጋፍ ተግባራት

የድህረ ሱፐርቪዥን ድጋፍ በርካታ ተግባራትን ያካትታል፡፡ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ሱፐርቫይዘሮች የክፍል ውጭና የክፍል ውስጥ ምልከታ ከተካሄደ በኋላ ማስታወሻቸውን በማየት የተረሱትን በመመዝገብ ማስታወሻቸውን የሚያስተካክሉበት ጊዜ ነው፡፡ እንዲሁም ከተጠሪ አመቻቾችና ከአመቻቾች ጋር የሚነጋገሩባቸውን ጉዳዮች በቅደም ተከተል መዝግበው የሚይዙበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በተገኙ መረጃዎች ከክፍል ውጭ"የክፍል ውስጥ ምልከታና የመረጃ ትንታኔ ከተካሄደ በኋላ አመቻቹ





ተጠሪ አመቻቹና ሌሎች ግምገማ የተካሄደባቸው አካላት ከሱፐርቫይዘሮች ጋር በመሆን በምልከታው ውጤት ላይ ይወያያሉ፡፡ የውይይቱ ዋና ዓላማ ሱፐርቫይዘሮች በምልከታው ወቅት ስላዩት የሥራ አፈፃፀም ለመነጋገር ሲሆን ተገምጋሚው ስለራሱ አፈፃፀም የሚረዳበትና ራሱን የሚያሻሽልበት እንዲሆን በጥንቃቄ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

ውይይቱ ማተኮር ያለበት ሱፐርቫይዘሮች ከክፍል ውስጥና ከውጭ በሰበሰቧቸው መረጃዎች ላይ ብቻ መሆን አለበት፡፡ ከብዙ ጥናቶች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት አመቻቾች ከሱፐርቫይዘሮች በሚያገኙት ምክርና መረጃ ብዙውን ጊዜ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎችን እንደሚቀይሩ ነው፡፡ የሚያደርጉት ለውጥ አወንታዊና ከሱፐርቫይዘሮች በተገኘው የምክርና ድጋፍ አገልግሎት አቀራረብ ጥራት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የተደረገው ግምገማዊ ውይይት ከተጠናቀቀ በኋላ ለወደፊት የትምህርት መስጫ ጣቢያው የሥራ አፈፃፀም እንዲሻሻልና ደካማ አሰራሮች ወደ ጠንካራ አሰራር እንዲቀየሩ የሪፖርቱ ቅጂ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ያስፈልጋል፡፡ ይህ የሚዘጋጀው ሪፖርት ሌሎችም ሊማሩበት የሚገባ በመሆኑ በወረዳው ወይም በክልሉ አማካኝነት ወደ አቻ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች እንዲላክ ያስፈልጋል፡፡ የሪፖርት አዘገጃጀቱንና አቀራረቡን በተመለከተ ምዕራፍ አምስትን መመልከት ይቻላል፡፡

የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቪዥን ከተከናወነ በኋላ የተሰጡ የድጋፍ ተግባራት ድጋፉን በወሰደው አካል ተፈፃሚ መሆናቸውን በተለያየ መንገድ ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ለዚህም የሚከተሉት ዘዴዎች ጠቃሚ ናቸው ፡፡

- በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ፣
- በየጊዜው ከጉዳዩ ባለቤቶች ጋር ውይይት በማድረግ፣
- ሪፖርቶችን በመቀበል ወይም በማዳመጥ፣
- የተቀናጁትንና የተደራጁትን የሱፐርቪዥን ሪፖርቶች መላልሶ በማየት፣
- በሱፐርቪዥን ዕይታ ውጤቶች ላይ በመመስረት የተሰጡ ውሳኔዎች ካሉ አፈፃፀማቸውን በመከታተልና በመገምገም ይከናወናል፡፡

በሌላ በኩል የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ባለድርሻዎችና የሱፐርቪዥን ድጋፍ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች (ተማሪዎች" ተጠሪ አመቻቾችና አመቻቾች) ሥራውን አስመልክተው በሚሰጡት ሃሳብና አስተያየት የሱፐርቪዥን ውጤቶች ተፈፃሚ መሆናቸውን በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡





# ምዕራፍ ሶስት

# ከአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ሱፐርቫይዘሮች የሚጠበቁ ተግባራት" ሥነምግባርና ክህሎት

እንደሚታወቀው አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች አስፈላጊው ግብዓት ሳይሟላላቸው በመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ያልታቀፉ ህጻናትን የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ከማድረግ አንጻር የተከፈቱ በመሆኑ ከመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም በተለየ መልኩ በተጠናከረ የሱፐርቪዥን አገልግሎት መደገፍ ይኖርባቸዋል፡፡ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን አገልግሎት በሚፈለገው መልኩ እንዲከናወንና በፕሮግራሙ የሚጠበቁ ውጤቶች እንዲገኙ ደግሞ የሱፐርቫይዘሮች ድርሻ የላቀ ነው፡፡ በመሆኑም ሱፐርቫይዘሮች ከሚኖራቸው ሥልጠናና የሥራ ልምድ አንፃር ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባራት"በአመራርም ሆነ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ሊኖራቸው

የሚገቡ ባህርያት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

## 3.1 የአማ/መሰ/ት/ሱፐርቫይዘሮች ተግባራት

የአማ/መሰ/ት/ሱፐርቫይዘሮች ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም መሳካት የሚያከናውኗቸው በርካታ ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፎች አሏቸው፡፡ ዋና ዋናዎቹ በሁለት ተከፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል&

### 3.1.1 ሙያዊ ድጋፍ

የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮች በትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ደረጃ የአመቻቾችን የትምህርት ደረጃ ዝቅተኛነትን እና የክህሎት ክፍተት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተጠሪ አመቻቾችና ለአመቻቾች የሚሰጧቸው ዋና ዋና የሙያ ድጋፍ ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የመማር ማስተማሩን ሂደት በማሻሻል ተፈላጊው ውጤት እንዲገኝ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ በመገኘት የተጠሪ አመቻቾችንና የአመቻቾችን ብቃት ያሳድጋሉ
- አመቻቾች በመማር ማስተማር ሂደት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በማሰባሰብና በመመርመር የመፍትሄ ሃሳቦችን ያፈልቃሉ "የሚመለከታቸውን በማሳተፍ ችግሮችን ይፈታሉ
- አዳዲስ የማስተማር ዘዴዎችን ያስተዋውቃሉ&ተግባራዊነታቸውን





ይከታተላሉ

- በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የሚሰጠው ትምህርት ጥራቱ የተጠበቀ የሚሆንበትን ተግባራዊ ስልቶች ይጠቁማሉ& ስለተግባራዊነታቸው ክትትል ያደርጋሉ
- ተማሪዎችን በተከታታይ ምዘና የመገምገምና የምዘናውን ውጤት በአግባቡ መዝግቦ የመያዝን ዘዴዎች ለአመቻቾች ያስገነዝባሉ
- አመቻቾችና ተጠሪ አመቻቾች ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር ልምድ የሚለዋወጡበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ
- ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ለአመቻቾች የሙያና የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጣሉ/ያመቻቻሉ
- አመቻቾችና ተጠሪ አመቻቾች ሥርዓተ ትምህርቱን እንዲገመግሙና የማሻሻያ ሃሳብ እንዲሰጡ ያበረታታሉ& ያስተባብራሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ የትምህርት ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስልቶችንና የትምህርት ሥራ መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላሉ እንዳስፈላጊነቱም የማሻሻያ ሃሳቦችን ያቀርባሉ

### 3.1.2 አስተዳደራዊ ተግባራት

የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮች በትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ደረጃ

የሚያከናውኗቸው ዋና ዋና አስተዳደራዊ ተግባራት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

- ለሚያከናውኗቸው የሱፐርቪዥን ተግባራት ቀደም ብለው ዕቅዶቻቸውን ያዘጋጃሉ
- የየጣቢያዎቹን አደረጃጀትና የአመራር ችግሮች በመለየት መፍትሄ እንዲያገኙ ያስተባብራሉ
- የትምህርት ቁሳቁሶችን አቅርቦትና አጠቃቀም"የአመቻቾች የስራ ድልድልና የሥራ ጫና&የበጀት አጠቃቀምን በሚመለከት ድጋፍ ያደርጋሉ ተግባራዊነቱንም ይከታተላሉ
- ህብረተሰቡ በትምህርት ሥራ ላይ ያለውን ተሳትፎ እንዲያጠናክር ድጋፍ ያደርጋሉ& በዚህም መሰረት አመቻቾች"ተጠሪ አመቻቾች"አስተባባሪዎች "ወላጆች "የአካባቢው አስተዳደርና የፖለቲካ መሪዎች በትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራቸው ያበረታታሉ& ያስተባብራሉ
- የክላስተር ማዕከላት ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የሚሰጡትን ሙያዊ ድጋፍ ያስተባብራሉ
- በመስክ ሥራ ወቅት ታይተው መፍትሄ ያልተገኘላቸውን ጉዳዮች & ለምሳሌ የሰው ኃይልና የቁሳቁስ አቅርቦት ማነስ የመሳሰሉትን በየደረጃው ከሚገኙና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር





መፍትሄ እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋሉ

- በየጊዜው ስለዕቅድ አፈፃፀማቸው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባሉ

## 3.2 ከአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮች የሚጠበቁ ሥነምግባራት

ከአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮች የሚጠበቁ የሥነምግባር እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አብረዋቸው ከሚሰሩ የትምህርት ባለሙያዎች"ተጠሪ አመቻቾች"አመቻቾች" የጣቢያው አመራር ኮሚቴዎችና ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር መልካም የሥራ ግንኙነት መፍጠር የሚችሉ
- በሙያቸው ጽኑ እምነት ያላቸውና በራሳቸው የሚተማመኑ
- በዲሞክራሲያዊ አሰራር የሚያምኑ
- አድልዎ የማያደርጉና በእኩልነት የሚያምኑ
- ሥነሥርዓትን በማስከበር ረግድ ለሌሎች አርዓያ የሚሆኑ
- ኃላፊነት የሚሰማቸው" ታታሪና በሥራ ክቡርነት የሚያምኑ
- ከጥላቻና ከስህተት ፈላጊነት የራቁ
- የራሳቸውን ፀባይ በመመርመር ጉድለታቸውን ለማረም ዝግጁ የሆኑ

- የሌሎችን ሃሳብ በአወንታዊ መልኩ የሚቀበሉና በሥራ አጋጣሚ ያወቋቸውን ሚስጢሮች የሚጠብቁ
- ለአመቻቾች ሙያዊ ድጋፍ የመስጠትና በመማር ማስተማር ሁኔታዎችን የማስተካከል ችሎታ ያላቸው
- ከግብታዊና ስሜታዊ አሰራር የራቁ"ነገሮችን በጥሞና የሚመለከቱ"ሁኔታዎችን በጥልቀት የሚመረምሩና በቂና ተጨባጭ ማስረጃ ሳይዙ አስተያየትና ውሳኔ ለመስጠት የማይቸኩሉ
- የኅብረተሰቡን አኗኗርና ባህል የሚያውቁና የሚያከብሩ እና የመሳሰሉት ናቸው;

## 3.3 የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮች ሊኖሯቸው የሚገቡ ክህሎቶች

የአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቫይዘሮች በየጊዜው ከሚወስዷቸው ሥልጠናዎችና ከሚኖራቸው የሥራ ልምዶች ሊያዳብሯቸውና ሊኖሯቸው ከሚገቡ ክህሎቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ሙያቸውን"ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በየጊዜው የሚያዳብሩ
- ኃሳብ አፍላቂዎችና ከስህተት ለመማር ዝግጁ የሆኑ
- ታጋሽ አዳማጭና ሁኔታዎችን የማገናዘብ ችሎታ ያላቸው





- የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲንና ስትራቴጂዎቹን እንዲሁም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራምን" ስታንዳርዱንና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶችን በሚገባ የሚያውቁ
- የማስተማር መርሆዎችንና ሥነ ዘዴዎችን" የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርትን ይዘቶችና የአፈፃፀም ደረጃ የሚያውቁና እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉ
- አስፈላጊ መረጃዎችን መሰብሰብ"ማደራጀት"መተንተንና ውሳኔ መስጠት የሚችሉ
- ማስተባበር" መምራትና መቆጣጠር የሚችሉ
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድና ጠቃሚ ባህሎች በአካባቢው እንዲዳብር አስፈላጊውን ጥረት የሚያደርጉ

## ምዕራፍ አራት

## የባለድርሻዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራምን ብቁና ውጤታማ በሆነ የሱፐርቪዥን አገልግሎት የመደገፉ ተግባር ለአንድ የተወሰነ አካል ብቻ የሚተው ሳይሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻዎች የተቀናጀ ጥረት እንዲሁም የቴክኒክ፣ የፋይናንስና የቁሳቁስ ድጋፍ የሚጠይቅ ነው። ይህን እውን ከማድረግ አኳያ በየደረጃው የሚገኙ አካላት የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 4.1. የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን በተቀናጀና ወጥነት ባለው መንገድ እንዲካሄድ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የክልል ትምህርት ቢሮዎችና ሌሎች ባለድርሻዎች በማሳተፍ የአተገባበር መመሪያ ያዘጋጃል፤ መመሪያው ሥራ ላይ መዋሉን በቅርብ ይከታተላል፤በትግበራው ሂደትም አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል።
- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ስታንዳርድና የአተገባበር መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤ በአፈፃፀም ላይም ሙያዊ ድጋፍ





ይሰጣል።

- የሱፐርቫይዘሮችን አቅም ከመገንባት አኳያ የሥራ ላይ ስልጠና ማኑዋሎችንና ጽሑፎችን ያዘጋጃል፤ የአሰልጣኞች ስልጠናም በማዕከል ደረጃ ይሰጣል።
- በአራቱም ታዳጊ ክልሎች ከፍተኛ የትምህርት ባለሙያዎችን በመመደብ ከክልል" ከወረዳና ከክላስተር ሱፐርቫይዘሮች ጋር መስክ ላይ አብረው እየሰሩ የሱፐርቫይዘሮችን አቅም እንዲገነቡ ያደርጋል።
- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን አፈፃፀምን ከየክልሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በየወቅቱ በመገምገም አገልግሎቱ የሚጠናከርበትን አቅጣጫ በጋራ ያስቀምጣል።
- አራቱ ታዳጊ ክልሎች በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን አፈፃፀም ዙሪያ የጋራ ውይይት የሚያካሂዱበት፣ መልካም ተሞክሮዎችን የሚለዋወጡበትና ላጋጠሙ የአፈፃፀም ችግሮች የጋራ መፍትሄ የሚሹበት መድረክ በማዕከል ያዘጋጃል።

### 4.2. የክልል ትምህርት ቢሮ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

- የክልሉን የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፣

- በማዕከል የተዘጋጀውን የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን አተገባበር መመሪያ የክልልና የወረዳ ባለድርሻዎችን በማሳተፍ ክልላዊ ያደርጋል፤ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤ በአፈፃፀም ላይ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል።
- ባለድርሻዎች በማሳተፍ ዓመታዊ የሱፐርቪዥን ዕቅድ፣ የዕቅድ ማስፈፀሚያ በጀትና የድርጊት መርሀግብር ያዘጋጃል በሚመለከተው አካል ያፀድቃል፤ተግባራዊ ያደርጋል፣
- የክልሉን የሱፐርቪዥን አገልግሎት ከማጠናከር አኳያ የቴክኒክ፣ የፋይናንስ እና የማቴሪያል (በተለይም የመጓጓዣ) ድጋፍ ከአጋር ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻዎች ያፈላልጋል።
- በክልሉ በሚገኙ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች አማካኝነት ሱፐርቫይዘሮች በክረምት የስልጠና መርሀግብር እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤ በሥልጠናው ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ሰልጣኞችን በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም ላይ በቂ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ይዘቶች መካተታቸውን ያረጋግጣል፤ በተመሳሳይ በሥራ ላይ ያሉ ሱፐርቫይዘሮች በኘሮግራሙ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ፣ የአተገባበር መመሪያዎችንና ስታንዳርድ ጠንቅቀው እንዲያውቁ ሥልጠና ይሰጣል። የአሰለጣጠን ሥነ ዘዴውም አሳታፊና ተግባር ተኮር መሆኑን ያረጋግጣል።
- በሥራ ላይ ላሉ ሱፐርቫይዘሮች በሥልጠና ፍላጐት ላይ የተመሠረተና





ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል። ወረዳዎች የአማ/መሠ/ትም/ሱፐርቪዥን አፈፃፀማቸውን በጋራ የሚገመግሙበት፣ መልካም ተሞክሮዎችን የሚለዋወጡበትና ላጋጠሙ የአፈፃፀም ችግሮች የጋራ መፍትሄ የሚሰጡበት መድረክ በክልል ደረጃ በየሩብ ዓመቱ ያዘጋጃል።

- በየሩብ አመቱ የሱፐርቪዥን ቡድኖች በማደራጀትና በክልሉ ወረዳዎች በማሰማራት በናሙናነት በተመረጡ የአማራጭ መሠ/ትም/ጣቢያዎች ተገኝተው የትምህርት እንቅስቃሴያቸውን እንዲገመግሙና አስፈላጊውን የሱፐርቪዥን ድጋፍ እንዲሰጡ ያደርጋል።
- የክልል ሱፐርቫይዘሮችንና የወረዳ ትም/ጽ/ቤቶች የሱፐርቪዥን ሪፖርቶችን መሠረት በማድረግ፣
- በክልል ደረጃ ሊፈቱ የሚገባ ችግሮችን በማቃለል የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ያጠናክራል፤
- መልካም ተሞክሮዎችን በማጠናቀር ለወረዳዎችና ለትም/መስጫ ጣቢያዎች ያሰራጫል

## 4.3 የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

- የወረዳውን የአማራጭ መሠ/ትም/ሱፐርቪዥን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፣
- ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻዎች በማሳተፍ የወረዳውን የአማ/መሠ/ትም ሱፐርቪዥን ዓመታዊ ዕቅድና ዕቅዱን የማስፈፀሚያ በጀት ያዘጋጃል፣ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ያፀድቃል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፣
- የሱፐርቪዥን አገልግሎትን ወደ ትምህርት መስጫ ጣቢያ የማውረዱ ኃላፊነት ባብዛኛው የወረዳ ትም/ጽ/ቤት የመሆኑን ያህል አገልግሎቱን በበቂ ሁኔታ መስጠት የሚችሉ ሱፐርቫይዘሮችን በወረዳና በክላስተር ማዕከል ደረጃ ይመድባል፤
- ከክልሉ ትምህርት ቢሮ ጋር በመነጋገር ለሱፐርቪዥን ሥራ የታጩ ባለሙያዎች የክረምት ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
- የጽ/ቤቱን ባለሙያዎች በመጠቀም ወይም የክልል ትምህርት ቢሮና የሌሎች ድርጅቶች ባለሙያዎች በመጋበዝ በፍላጐት ላይ የተመሠረተ ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለክላስተር ሱፐርቫይዘሮች ይሰጣል፤
- የወረዳውን የሱፐርቪዥን አገልግሎት ለማጠናከር የቴክኒክ፣ የፋይናንስና የማቴሪያል ድጋፍ በወረዳው ከሚሰሩ አገር በቀልና ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻዎች





ያፈላልጋል፤

- በት/ቤቶች ጉድኝት መመሪያ መሠረት ቋሚ አማ/መሠ/ት/ጣቢያዎችን ከመደበኛ መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ጋር በክላስተር ያደራጃል፤
- የክላስተር ማዕከሉ ሱፐርቫይዘር በየ15 ቀኑ በእያንዳንዱ ትምህርት መስጫ ጣቢያ በመገኘት የሱፐርቪዥን አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል። ከዚህም በተጨማሪ ጣቢያዎቹ ከክላስተር ማእከሉ የቁሳቁስና የሙያ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
- በርቀት ወይም በተንቀሳቃሽ ባህሪያቸው ምክንያት በክላስተር ሊደራጁ የማይችሉ ቋሚና ተንቀሳቃሽ አማ/መሠ/ትም/ጣቢያዎችን በተመለከተ እያንዳንዱ ጣቢያ በየወሩ የ2 ቀናት የሱፐርቪዥን ድጋፍ በጽ/ቤቱ ሱፐርቫይዘሮች አማካኝነት እንዲያገኙ ፤
- ሱፐርቫይዘሮች የሚያቀርቧቸውን ሪፖርቶች መሠረት በማድረግ
- በወረዳ ደረጃ ሊፈቱ የሚገባቸውን ችግሮች እንዳስፈላጊነቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መፍትሄ እንዲያገኙ እያደረገ አማ/መሠ/ ትምህርት ፕሮግራምን ያጠናክራል፤ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ሁኔታ እየገመገመ ወደ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እንዲያድጉ ያደርጋል፤
- በአንዳንድ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር በሌሎች ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

- በትምህርት መስጫ ጣቢያ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችና የማስተካከያ እርምጃዎች ሥራ ላይ ስለመዋላቸው በሱፐርቫይዘሮች አማካኝነት ክትትል ያደርጋል፤
- የወረዳውን የሱፐርቪዥን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ወርሀዊ ሪፖርት ለክልሉ ትምህርት ቢሮ ያቀርባል።

## 4.4. መንግሥስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

በአማ/መሠ/ትምህርት ሱፐርቪዥን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኘሮግራምን የሚተገብሩም ሆነ ተባባሪ የሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድርሻ ሰፊ ነው። በመሆኑም ፡-

- የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ይሰጣሉ፤
- ለሱፐርቪዥን አገልግሎት ግብዓት በማሟላትና ለሱፐርቫይዘሮች ሥልጠና በመስጠት ድጋፍ ያደርጋሉ፤
- የሱፐርቪዥን ውጤቶች ተዘንግተው እንዳይቀሩ ይከታተላሉ፤
- ከተለያዩ የትምህርት አመራርና ባለሙያዎች ጋር በጋራ በማቀድ"በመተግበርና በመገምገም ይሳተፋሉ፤
- የሱፐርቪዥን ዕቅድ ትግበራው ውጤታማ እንዲሆን በማስተባበርና ለችግሮች የመፍትሄ ሃሳቦችን በማፍለቅ ይሳተፋሉ፤





- ለሚመለከታቸው የትምህርት መዋቅራት በየወቅቱ በሚያቀርቧቸው የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ ስላከናወኗቸው የሱፐርቪዥን ተግባራት አካተው ያቀርባሉ።

## 4.5. የቀበሌ ትምህርትና ሥልጠና ቦርድ /የጣቢያ ትምህርት አመራር ኮሚቴ/የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የቀበሌ ትምህርትና ሥልጠና ቦርድ በቀበሌው ያለውን የትምህርት ሥራ በበላይነት የሚመራ አካል ነው። ስለዚህም ቦርዱ የአማ/መሰ/ት/ ሱፐርቪዥን አገልግሎት አተገባበርን በመከታተልና የሱፐርቪዥን አገልግሎትን በማከናወን ግምባር ቀደም ሆኖ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

በመሆኑም፡-

- ኅበረተሰቡን"መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን በማስተባበር፤
- የክትትል፣የግምገማና የድጋፍ መርሃ ግብሮች እንዲዘጋጁ ሁኔታዎችን በማመቻቸት፤
- የአማ/መሰ/ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ግምገማ ላይ ህብረተሰቡን በማንቃትና በማሳተፍ፤
- በሚቀርቡት የሱፐርቪዥን ሪፖርቶች መሰረት በውጤቶች ላይ የጋራ ውሳኔ በመስጠት

- ለውሳኔው ተግባራዊነት ከህብረተሰቡና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

## 4.6. የአመቻቾች የሥራ ኃላፊነት

አመቻቾች ተማሪዎቻቸውን ከማስተማር በተጨማሪ በአማ/መሰ/ት/ሱፐርቪዥን አገልግሎት ተሳታፊ ናቸው። ይኸውም፡-

- በሱፐርቪዥን ወቅት በሥራቸው ሂደት ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለውይይት በማቅረብና የበኩላቸውን የመፍትሄ አቅጣጫዎች በመጠቆም
- የተሻለ የትግበራ አፈፃፀም መንገዶች እንዲስፋፉ እገዛ በማድረግ
- ከሱፐርቪዥን ድጋፍ ያገኙትን ልምድ መሰረት በማድረግ የወደፊቱን ሥራ በአግባቡ አቅደው ለመስራት ጥረት በማድረግ፣
- የሱፐርቪዥን መረጃዎች በአግባቡ ተመዝግበውና ተደራጅተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ
- በሱፐርቪዥን አገልግሎት የአካባቢው ማህበረሰብ እንዲሳተፍ በማስተባበር
- በአጠቃላይ ከዕቅድ ማውጣት እስከ ሪፖርት ማቅረብና የሱፐርቪዥን ውጤቶችን ማሰራጨት ድረስ ከሱፐርቫይዘሮች ጋር አብረው በመስራት





ይሳተፋሉ።

## 4.7. የመደበኛ ትምህርት ቤቶች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

መደበኛ ትምህርት ቤቶች (የክላስተር ማዕከላትና ሳተላይት ትምህርት ቤቶች) በተለያየ መልኩ ለአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቪዥን አገልግሎት መሳካት የበኩላቸውን ያበረክታሉ። ከሚያከናውኗቸው እገዛዎች መካከል፡-

- አመቻቾችን በማሰልጠንና በመደገፍ፤
- የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀትና በማዋስ፤
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የጉድኝት ማዕከል በመሆን፣
- በአቅራቢያቸው ባለው አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ በመገኘት የሱርቪዥን አገልግሎት በማካሄድ የሱፐርቪዥን ውጤቶችንና ተጨባጭነት ያለው መረጃ ለወረዳው ት/ጽ/ቤት በማቅረብ፤
- የተሻለ የዕቅድ አፈፃፀም ዘዴዎች በአካባቢያቸው ባሉ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች እንዲስፋፉ የበኩላቸውን እገዛ ማድረግና የመሳሰሉት ጉልህ የሆኑ አስተዋጽኦ የሚያደርጉባቸው ተግባራት ናቸው።

## 4.8. የአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

በመጀመሪያ ደረጃ የማንኛውም ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ተጠቃሚ

ህብረተሰቡ ነው። የአማ/መሰ/ትም/ፕሮግራምም በዋነኝነት ተጠቃሚው የአካባቢው ማህበረሰብ ነው። ስለሆነም በአማ/መሰ/ትም/ሱፐርቪዥን ድጋፍ የሚገኘው ውጤት የህብረተሰቡ ልጆች ተጠቃሚ ያደርጋል። ከዚህ አኳያ የህብረተሰቡ ድርሻ በሚከተሉት ሀሳቦች ላይ ያተኩራሉ።

- ለሱፐርቪዥን አገልግሎት ትግበራ ከማቀድ እስከ ፍፃሜው ድረስ የጎላ ተሳትፎ በማድረግ፣

## ምዕራፍ አምስት

## የአማ/መሰ/ት/ሱፐርቪዥን ግምገማ ሪፖርት አቀራረብ

ሪፖርት የተወሰነ ሕግና ሥርዓትን በመከተል አንድን የተከናወነ ወይም በመከናወን ላይ ያለን ተግባር አፈፃፀም (የክንውን ደረጃ) ለሚመለከተው (ውሳኔ ሰጭ) አካል መረጃ የሚቀርብበት የአሰራር ሂደት ነው፡፡ አፈፃፀሙም ከስሜታዊነትና ከወገናዊነት ነፃ ሆኖ በተጨባጭ መረጃና እውነታ ላይ በመመመስረት የሚደራጅና የተቋሙን (የሥራ ክፍሉን) ትክክለኛ ገጽታ ለማሳየት የሚረዳ የሥራ አመራር መሳሪያ ነው፡፡ የሱፐርቫይዘሮች ዋነኛ ተግባር የትምህርት ተቋማትን የሥራ እንቅስቃሴ በመከታተልና በመገምገም ድጋፍ መስጠትና ብሎም ሪፖርት ማዘጋጀት ነው፡፡ በመሆኑም ሱፐርቫይዘሮች የሪፖርት አቀራረብ ስልትን የተከተለ ሪፖርት ማዘጋጀት የሚያስችላቸውን





ግንዛቤ የሚያስጨብጥ የሪፖርት አዘገጃጀት ማብራሪያ በዚህ የሱፐርቪዥን መመሪያ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

የሱፐርቪዥን ሪፖርቱ የሚላከው ለበላይ አካል ብቻ ሳይሆን ከጥንካሬም ሆነ ከድክመት የሚማሩበት እንዲሆን ለሌሎች አቻ አማ/መሠ/ትም/መስጫ ጣቢያዎችም በመሆኑ ሪፖርቱ በአግባቡ መዘጋጀት አለበት። አንድን ሪፖርት ትክክለኛ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል ሪፖርቱ ሲዘጋጅ ፡-

- ጉዳዩን በቀጥታ በማየት
- ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ
- በልምድ ከተገኙ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ
- ስለጉዳዩ ጠለቅ ያለ ምርምር በማካሄድና ማስረጃዎችን በአግባቡ መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣መተነተን፣ እንዲሁም
- ለአጋጠሙ ችግሮች መፍትሄዎችን መግለጽ ሲቻል ነው

### 5.1 ሪፖርት አቅራቢዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ጉዳዮች

በሪፖርት አቀራረብ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ አቅራቢዎች ሪፖርት የሚያቀርቡበትን ጉዳይ ጠንቅቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ሪፖርት አቅራቢዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች በጥንቃቄ ማከናወን

ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ከንውኖችን በትክክል በማስተዋል ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውንና የሌላቸውን ለይተው በየመልካቸው ማቅረብ
- ከሁሉ በፊት ነገሮችን እንዳሉ ማየትና ማስተዋል መቻል አስፈላጊ ሲሆን የታዩትን መገምገምና መተንተን
- አስቀድሞ ሁኔታዎች ይህን ይመስላሉ ወይም ሊመስሉ ይችላሉ ብሎ በመተንበይ አቋም መያዝ አያስፈልግም፡፡አስቀድሞ የታሰበውና በዓይን የታየው ልዩነት ኖሯቸው የሃሳብ መጋጨት እንዳይከሰት በአዲስ መልክ ድርጊቱን በማየት መገምገም
- በጥሩ ልምድ"ዕውቀትና ማስተዋል ላይ የተመሰረተ ግምገማ ጥሩ አቀራረብ ስለሚያስፈልገው ያለውን ሁኔታ በግልፅ ማስረዳት የሚችል መሆን አለበት

## 5.2 ሪፖርት መፃፍ ከመጀመሩ በፊት መታወቅ ያለባቸው ጉዳዮች

የሱፐርቪዥን አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች ስለሥራቸው አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ የግድ ስለሚል የሚከተሉትን የሪፖርት አፃፃፍና አቀራረብ ወሳኝ ተግባራት መከተል ያስፈልጋቸዋል፡፡





- መረጃ በመስጠትና የመረጃዎችን ትክክለኛነት በመመርመር፣
- በሱፐርቪዥን ሪፖርቶች የራሱን አስተያየትና ውሳኔ በመስጠት፣
- በውሳኔዎች ተግባራዊነት ላይ የክትትልና ድጋፍ ስልት ቅየሳ ላይ በመሳተፍ፣
- በአጠቃላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር የአማ/መሰ/ት/ሱፐርቪዥን አገልግሎት ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆን የበኩላቸው ይወጣሉ።

## 4.9. የአማ/መሰ/ትምህርት ተማሪዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የአማ/መሰ/ትምህርት ተማሪዎች የፕሮግራሙ ዋነኛ ተጠቃሚዎች ናቸው። ስለዚህም በጣቢያቸው ለሚከናወኑ የሱፐርቪዥን ተግባራት ሀሳብ በመስጠት፣ ጠንካራና ደካማ አሰራሮችን ለይቶ በማመልከት፣ ወዘተ… ለሱፐርቪዥኑ ውጤታማነት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

### ሀ) የሪፖርት አድማጩን ወይም ተቀባዩን ማንነት መለየት

ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ ሪፖርት ከመፃፉ በፊት ሪፖርቱ የሚቀርብለትን አካል አጠቃላይ ሁኔታ መለየትና ማወቅ ወይም መገመት ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ አካላት በአንድ ዓይነት ጉዳይ ላይ ያላቸው አቋምና አመለካከት ሊለያይ ስለሚችል ሪፖርት አቅራቢዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከግንዛቤ ቢያስገቡ ለሚያቀርቧቸው ሪፖርቶች መነሻ ይሆኗቸዋል፡፡

- የሚቀረበው ሪፖርት በጣቢያ ደረጃ ለማስረጃነት የሚያገለግል ወይም ከዚያም አልፎ ሊሄድ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ
- ሪፖርቱን የሚያነቡት/የሚያዳምጡት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ብቻ ወይም ሌሎችም የሚገኙበት ለመሆኑ መለየት
- ለሪፖርቱ መቅረብ ዋናው ምክንያት ምን እንደሆነ ማወቅ
- ሪፖርቱ ለአንድ ጊዜ ወይም በየጊዜው የሚቀርብ ወይም ለልዩ ዝግጅት የሚቀርብ መሆኑን መለየት
- ሪፖርቱ እንዲቀርብ በሌላ ክፍል ተጠይቆ ወይም በአቅራቢው ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ ማወቅ
- የሚቀርበው ሪፖርት ለተቀባዩ አካል የሚሰጠው ጥቅም ምን መሆን እንዳለበት በቅድሚያ መታወቅ ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡





### ለ) የሪፖርቱን ዓላማና ይዘት በአጭሩ መግለጽ የሚያስችል ርዕስ መምረጥ

የተመረጠውን ትክክለኛ ርዕስ ማስፈር ከተቻለ ሪፖርቱ ያስፈለገበትን ዐቢይ ምክንያት"የሪፖርቱን ዓይነትና አቀራረብ እንዲሁም ሊጠቀሱ የሚገባቸውን ፍሬ ነገሮች ከርዕሱ መተለም ይቻላል፡፡ ከዚህም በመነሳት፡-

- የሪፖርቱን ቅርፅ
- የሪፖርቱን የአቀራረብ ስፋት በመወሰን
- የሚቀርበው ሪፖርት አጠር ያለ ማስታወሻ ወይስ ረዥም መሆን አለበት ብሎ መወሰን ያስችላል፡፡ ስለዚህ አንባቢው/አድማጩ የሪፖርቱን ዓላማ ምንነት ከርዕሱ በመረዳት ዝርዝሩን ለመከታተል ይረዳዋል፡፡

### ሐ) ሪፖርቱ የሚያነጣጥርባቸውን ዋና ዋና የሃሳቦች አስተዋፅኦ መንደፍና ማቀነባበር

ለሪፖርት አፃፃፍ በቅድሚያ ዕቅድ በማውጣት ሪፖርቱ የሚያቅፋቸውን የትኩረት አቅጣጫዎች እንደቅደም ተከተላቸው መንደፍና ማቀነባበር አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡

## 5.3 የሪፖርት ዋና ዋና ክፍሎች

## ሀ) የሪፖርቱ መግቢያ

- በዚህ ክፍል ውስጥ ስለሪፖርቱ መቅረብ መንስዔ የሆነው ዋናው ችግር ወይም ምክንያት መግለፅ
- የጉዳዩን ምንነት"ጥልቀትና ስፋቱን እንዲሁም ዓላማውን መግለፅ& በዚህ ሥር ከሚጠቀሱት መካከል፡-
    - ◊ ሪፖርቱ ስለቀረበበት ጉዳይ የተደረገ ጥናት ወይም ጉብኝት"አጥኚው ቡድን ወይም ጎብኚው ማን እንደሆነ ወይም እነማን እንደሆኑ"መቼ እንደተደረገና ምን ያህል ጊዜ እንደፈጀ መጥቀስ
- የሪፖርቱ ይዘት የሚያተኩርባቸው ዓበይት ነጥቦች በአጭሩ መግለጽ"በተለይ አሳሳቢና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ሃሳቦችን ለይቶ ማመልከት
- የመረጃ አሰባሰብ ስልት እንዴት እንደሆነ መግለጽ&በዚህም
    - ◊ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር ውይይት በማድረግ
    - ◊ የጽሁፍ መረጃ በመሰበሰብ
    - ◊ አፈፃፀሙን በድርጊት በማየት
    - ◊ ቅጾችን በማስሞላት … ወዘተ ከመሳሰሉት ስልቶች





ሪፖርት አቅራቢ በየትኛው እንደተጠቀመ ከዚህ አኳያ ያጋጠሙ ችግሮች ካሉ የሚገለፅበት ክፍል ነው ፡፡

## ለ) የሪፖርቱ አካል

በዚህ ክፍል ሪፖርቱ ስለቀረበበት ጉዳይ ጠቅላላ ገጽታ በዝርዝር የሚገለፅበት ሲሆን ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ሪፖርቱ ስለቀረበበት ጉዳይ ከአሁን በፊት የሚታወቅ ታሪኩን መጥቀስ"ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰና ያሳለፋቸውን የዕድገት ደረጃዎች ማመልከት
- የተከሰተ ችግር ካለ ምክንያቱንና ውጤቱን"በዚህ ሳቢያ የደረሰ ጉዳት ካለ፣
- ጉዳዩን አስመልክቶ ድክመቱንና ጥንካሬውን በየመልኩ በመለየት፤ ለድክመቱና ለጥንካሬው አስተዋፅዖ ያደረጉ ምክንያቶች ምን እንደሆኑ"በአጠቃላይ ስለጉዳዩ የሚታወቁ ሁኔታዎች በሙሉ የሚተነተኑበት የሪፖርቱ ሰፊ ክፍል ነው፡፡

## ሐ) የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች (Lessons Learnt)

ከሱፐርቪዥን የተገኙና ለሌሎች አቻ አማ/መሠ/ትም/መስጫ ጣቢያዎች

ሊተላለፉ የሚችሉ ጥሩ ልምዶችና መልካም ተሞክሮዎችን የሚዘረዘሩበት የሪፖርቱ ክፍል ነው፡፡

**መ) ማጠቃለያ**

ይህ ክፍል በዝርዝር ከቀረቡት ሃሳቦች ውስጥ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ የታየ ድክመትና ጥንካሬዎችን ክብደት በማመዛዘን አንገብጋቢ የሆኑ ነጥቦችን ከሪፖርቱ ለይቶ በማውጣት ለጉዳዩ ምን ያህል ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ማመልከትና የሪፖርቱ መደምደሚያ ሃሳብ የሚቀርብበት ክፍል ነው፡፡

**ሠ) የሪፖርት አቅራቢው አስተያየት**

ሪፖርት አቅራቢዎች በተቻለ መጠን ሪፖርት ስለቀረቡበት ጉዳይ የራሳቸውን አስተያየት እንዲያክሉበት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ለተከሰቱ ችግሮች በሪፖርት አቅራቢው አመለካከት መፍትሄ ናቸው የሚላቸውን"ጉዳዩ አሳሳቢ ከሆነ መደረግ ስላለበት ለውጥ"መቀየስ ስላለበት ታክቲክና ስትራቴጂ የሚጠቁምበት ክፍል ነው፡፡ ስለዚህ የሪፖርት አቅራቢው አስተያየት ከራሱ

ግንዛቤና ምርምር የሚመነጭ "ነፃ የሆነ የግለሰቡ አመለካከት ነው ፡፡

## 5.4 በሪፖርት አፃፃፍ ላይ መሰረታዊ መመሪያዎች

ትክክለኛ ሪፖርት የስሜትና የግል ሃሳብ መግለጫ ሳይሆን የሂደቶች ትክክለኛ





ገጽታ የሚመዘገብበት ቋሚ ማስረጃ ነው፡፡ ስለሆነም ሪፖርት ተቀባዩ የሚያስፈልገውን መረጃ ግልጽና ቀለል ባለ ዘዴ እንዲረዳው ለማድረግ ሪፖርት አቅራቢው የሚከተሉትን ሃሳቦች እንደ መመሪያ ቢጠቀምባቸው ጥሩ ውጤት ይኖረዋል፡፡

**ሀ) የሚቀርበው ሪፖርት የአንባቢውን ጊዜ የሚቆጥብ መሆን አለበት**

ይውም ፡-

- ጽሁፉ በግለፅ እንዲነበብ በማድረግ
- የዐረፍተነገሮችና የሃሳቦችን መደጋገም በማስቀረት
- ሃሳብን ቀለል ባለሉ ዐረፍተነገሮች መግለጽ
- የመረጃውን አቀራረብ በተመለከተ፡- አኃዛዊ መረጃዎች በጣቢያ ዓይነት፣ በጾታ፣ በደረጃ የሚቀርብ ሲሆን ሌሎች መረጃዎች ከዕቅድ ክንውን አካያ በዝርዝር የሚቀርቡ መሆን አለባቸው፣
- የማውጫው ቅደም ተከተል ትክክል ሆኖ ዋና ርዕሶች ከንዑሳን ርዕሶች ጋር ውህደት እንዲኖራቸው በማድረግ
- የሪፖርቱን ፍሬ ነገሮች ያዘሉ ማጠቃለያ ሃሳቦች በተገቢው ቦታ በተለይ በመጀመሪያ ላይ በማስገባት
- እያንዳንዱ አንቀጽ የራሱ መንደርደሪያ እንዲኖረው በማድረግ ወዘተ የእነዚህ ሁኔታዎች መሟላት እንባቢው የሚፈለገውን በአጭር ጊዜ

እንዲያገኝ ይረዱታል፡፡

**ለ) ሪፖርቱ ተጨባጭ እንዲሆን ማድረግ**

በሪፖርት አፃፃፍ ሪፖርቱ ስለሚያወራው ጉዳይ የሚገልጹ ነገሮች ሁሉ ከሪፖርት አቅራቢው ስሜትና መልካም ፍላጎት የሚመነጩ ሳይሆኑ የነገሩን ሂደት"ውጤትና የተገኙት ተጨባጭ ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡

**ሐ) ሁኔታዎችን አጋኖ አለማቅረብ**

በሪፖርቱ ላይ የሚሰፈሩ ሃሳቦች በሳይንስና ግምገማ ላይ ሊመሰረቱ ይገባል፡፡ ከግምት ውጭ ወይም በተግባር የማይታይን ነገር ከማጋነን ይልቅ ነባራዊ ሁኔታንና ትክክለኛ ግምትን ማቅረብ ይመረጣል፡፡

**መ) ሪፖርትን በሰንጠረዥና በቻርት ማቅረብ**

በቃላት ለመግለጽ ሰፊ የሆኑትን ነገሮች በአጭሩ ለመግለጽ ሰንጠረዥና ቻርት መጠቀም ይገባል; ሆኖም ግን ብቻቸውን በቂ መልዕክት ስለማያስተላልፉ ከሰንጠረዡ ውስጥ ጎላ ብሎ የሚታየውን መርጦ ማብራሪያ መስጠት ይገባል፡፡

**O) አከራካሪ በሆነ ጉዳይ ላይ የሪፖርት አቅራቢው አስተያየት**





ሪፖርት አቅራቢዎች አከራካሪ በሆነ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን ሲያቀርቡ ምክንያታዊና አድልዎ የሌለበት ነፃ የሆኑበትን አቋማቸውን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**ለ) ሪፖርቱ ተጨባጭ እንዲሆን ማድረግ**

በሪፖርት አፃፃፍ ሪፖርቱ ስለሚያወራው ጉዳይ የሚገልጹ ነገሮች ሁሉ ከሪፖርት አቅራቢው ስሜትና መልካም ፍላጎት የሚመነጩ ሳይሆኑ የነገሩን ሂደት"ውጤትና የተገኙት ተጨባጭ ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡

**ሐ) ሁኔታዎችን ኢጋኖ አለማቅረብ**

በሪፖርቱ ላይ የሚሰፈሩ ሃሳቦች በሳይንስና ግምገማ ላይ ሊመሰረቱ ይገባል፡፡ ከግምት ውጭ ወይም በተግባር የማይታይን ነገር ከማጋነን ይልቅ ነባራዊ ሁኔታንና ትክክለኛ ግምትን ማቅረብ ይመረጣል፡፡

**መ) ሪፖርትን በሰንጠረዥና በቻርት ማቅረብ**

በቃላት ለመግለጽ ሰፊ የሆኑትን ነገሮች በአጭሩ ለመግለጽ ሰንጠረዥና ቻርት መጠቀም ይገባል; ሆኖም ግን ብቻቸውን በቂ መልዕክት ስለማያስተላልፉ ከሰንጠረዡ ውስጥ ጎላ ብሎ የሚታየውን መርጦ ማብራሪያ መስጠት ይገባል፡፡

**ሠ) አከራካሪ በሆነ ጉዳይ ላይ የሪፖርት አቅራቢው አስተያየት**

ሪፖርት አቅራቢዎች አከራካሪ በሆነ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን ሲያቀርቡ ምክንያታዊና አድልዎ የሌለበት ነፃ የሆኑበትን አቋማቸውን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

አባሪ

**የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ሱፐርቪዥን ቼክ ሊስት (ለመነሻ የቀረበ)**

# I. የጣቢያው አጠቃላይ ሁኔታ

የጣቢያው ሥም ____________________________

ጣቢያው የታቀፈበት የጉድኝት ማዕከል ሥም _______________

የጣቢያው ዓይነት (በ “X” ምልክት ያሳዩ)፡

- ቋሚ
- ተንቀሳቃሽ

የትምህርት መስጫ ☐ ቋንቋ _________

የጠቢያው የገቢ ምንጭ፡

ከመንግሥት ☐ ከህብረተሰብ

ከአጋሮች ከውስጥ ገቢ

ከሁሉም በጀት የለውም

የጠቢያው ☐ አጠቃላይ የገቢ መጠን /በብር ☐ ይገለጽ/፡

☐ ☐ ብር_________

## 1. ቋሚ ጣቢያ ☐ ☐

**የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያው፡**

ከተማሪዎች መኖሪያ ቤት በአማካይ ያለው ርቀት (በ “X” ምልክት ያሳዩ)፤

ከ3 ኪሜ በታች 3 ኪሎ ሜትር

ከ3 እስከ 4ኪሜ ከ4ኪሜ በላይ

የግቢ ስፋት ☐ (በካሬ ሜትር ይገለጽ)፤ ☐





_________ ☐ ☐

የመጫወቻ ሜዳ፤ አለው የለውም

በህፃናት ላይ አደጋ ☐ ሊያስከትሉ ከሚችሉ ☐ ነገሮች (አውሬ፣ ገደል፣ ጎርፍ ወዘተ) የራቀ ነው? አዎ አይደለም

**በትምህርት መስጫ ጣቢያው ☐ መኖር የሚገባቸው አገልግሎቶች፡**

የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች

መማሪያ ክፍል፣ አለ የለም

መልሱ “**አለ**” የሚል ከሆነ ☐ ስንት ክፍሎች ☐ አሉት? (በቁጥር ይገለጽ)

☐ የክፍል ስፋት (በካሜ ☐ ይገለጽ) _________

የአመቻቾች ቢሮ፣ አለ ☐ የለም ☐

የእቃ ግምጃ ቤት፣ አለ ☐ የለም ☐

መፀዳጃ ቤት፤ አለ የለም ☐

**ካለ** የወንድና የሴት፡ የተለየ ነው፡፡ ☐

☐ አንድ ላይ ☐

☐ ነው፡፡ ☐

የውሃ አገልግሎት፣ አለ የለም

የሕፃናት መጫወቻ ሜዳ፣ አለ የለም

አጥር ☐ (በአካባቢው በቀላሉ ☐ ከሚገኝ ቁሳቁስ የታጠረ)፡

አለ የለም

**የመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች የተሠሩባቸው ቁሳቁስ** (በ "X" ምልክት ያሳዩ)፡

- በአካባቢው ከሚገኙ የግንባታ ቁሳቁሶች እንደ እንጨት፣ ጭቃ፣ ጡብና ድንጋይ ከመሳሰሉት ነው፡፡
- ከፋብሪካ ውጤቶች ነው ፡፡

**የትምህርት መስጫ ጣቢያው የተሰራው** (በ "X" ምልክት ያሳዩ)፤

በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ አጋር ድርጅቶች

በአካባቢ ሕብረተሰብ በሁሉም ትብብር

## 2. የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት፤

**የትምህርት መስጫ ጣቢው፡**

የሚማሩ ህፃናት ብዛት፣ ወንድ _____ ሴት _____ ድምር _____

ህፃናትን ለአደጋ ከሚያጋልጡ ሁኔታዎች፣

የራቀ ነው የራቀ አይደለም

ለህፃናቱ የመጫወቻ ቦታ አለው የለውም

ውሃ አለው የለውም





በጣቢያ ትምህርት የሚሰጠው፡- በድንኳን ነው

በዳስ ነው

### ሀ. በድንኳን የሚሰጥ ከሆነ፣

**የድንኳኑ አሠራር፡**

በቀላሉ ከቦታ ቦታ ሊንቀሳቀስና ሊገጣጠም የሚችል፣

ነው አይደለም

በቂ አየር የሚያስገባ ነው? አዎ

አይደለም

ቀለሙ የአካባቢውን የአየር ንብረት ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ ነው?

አዎ አይደለም

በአገር ውስጥ የተመረ ነው? አዎ አይደለም፣

**የድንኳኑ መጠንና የመያዝ አቅም**

የድንኳኑ ስፋት (በካሜ የገለጽ) _________

ድንኳኑ ማስተናገድ የሚችለው የተማሪዎች ብዘት (በቁጥር ይገለጽ) ______

በድንኳኑ እየተማሩ ያሉ ተማሪዎች ብዛት (በቁጥር ይገለጽ) _________

### ለ. በዳስ የሚሰጥ ከሆነ የዳስ መጠን፡

የዳሱ ስፋት (በካሬ ሜትር ይገለጽ) ፣ _________

የዳሱ ተማሪዎችን የመያዝ አቅም (በቁጥር ይገለጽ)፣ ________

ዳሱ በጥንቃቄ/ አደጋ በማያስከትል ሁኔታ የተሠራ ነው?   አዎ     አይደለም

## II. አስፈላጊ የትምህርት ቁሳቁሶች፣ የመማሪያ መጽሐፍት፣ መመሪያዎችና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡

### 1. ቋሚ የአማራጭ ትምህርት መስጫ ጣቢያ

**ሀ) የመመሪያ ክፍል ቁሳቁሶች፤**





| ተ ቁ | የዕቃው ዓይነት | አለ / የለም | ካለ ያለበት ደረጃ ስታንዳርዱን የጠበቀ/ያልጠበቀ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዴስክ / ከነመቀመጫው/ | | | |
| 2 | አግዳሚ ማስደገፊያ / ተስተካክሎ የተጠረበ እግር ያለው ጣውላ / | | | |
| 3 | አግዳሚ መቀመጫ / የተጠረበ ጣውላ / | | | |
| 4 | ጠረጴዛ | | | |
| 5 | ወንበር | | | |
| 6 | ጥቁር ሰሌዳ | | | |
| 7 | ማስታወቂያ ሰሌዳ | | | |

**ለ) በአመቻች ቢሮ መኖር ያለባቸው ቁሳቁሶች፡**

| ተ ቁ | የዕቃው ዓይነት | አለ / የለም | ካለ ያለበት ደረጃ ስታንዳርዱን የጠበቀ/ያልጠበቀ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አግዳሚ መቀመጫ | | | |
| 2 | ባለ ኪስ ጠረጴዛ | | | |
| 3 | ባለ መደገፊያ ደረቅ ወንበር | | | |
| 4 | የተለያዩ ሰነዶች መደርደሪያ | | | |

☐ ☐

**ሐ) በዕቃ ግምጃ ቤት መኖር ያለበቸው ቁሳቁሶች፣**

የመጽሐፍ መደርደሪያ - አለ የለም

**መ) የመጫወቻ ቁሳቁስ፤**

የመረብ ኳስ - አለ የለም

መረብ አለ የለም

የእግር ኳስ - አለ የለም

ባህላዊ የመጫወቻ መሳሪያዎች አለ የለም

ለባህላዊ መሣሪያዎች መልስዎ "**አለ**" ከሆነ ምሣሌ ይጥቀሱ፤

1. ___________________________
2. ___________________________
3. ___________________________

ሌላ ____________________

**ሠ) የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍት፣**

**<u>የተማሪ-- መጽሐፍ ጥምርታ</u>**

| <u>የመጽሐፉ ዓይነት</u> | <u>ጥምርታ</u> |
|---|---|
| አፍ መፍቻ ቋንቋ | _____ |
| እንግሊዝኛ | _____ |
| ሂሳብ | _____ |





| | |
|---|---|
| የአካባቢ ሣይይንስ | _____ |
| **አማካይ** | _____ |

**ረ) ልዩ ልዩ መመሪያዎችና ደንቦች፤**

| ተቁ | የመመሪያው ዓይነት | አለ | የለም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የአጠቃላይ ትምህርት ፖሊሲ፣ | | | |
| 2 | የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ፣ | | | |
| 3 | የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአነስተኛ ጥራት መለኪያ ማኑዋል፣ | | | |
| 4 | ለአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር አካባቢዎች የተዘጋጀ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አተገባበር መመሪያ፣ | | | |
| 5 | የተንቀሳቀሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አተገባበር መመሪያ፣ | | | |
| 6 | የት/ቤቶች ተጨማሪ በጀት መመሪያ (School grant manual)፣ | | | |
| 7 | ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት አተገባበር መመሪያ፣ | | | |
| 8 | የሴቶች ትምህርት ስትራቴጂ፣ | | | |
| 9 | የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ | | | |
| 10 | የየትምህርቱ ዓይነት መርሀ ትምህርቶች፣ | | | |
| 11 | የመምህሩ መምሪያዎች በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣ | | | |
| 12 | የተማሪው መጽሐፍ በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣ | | | |
| 14 | የትምህርት ካሌንደር፣ | | | |
| 15 | የልዩ ፍላጐት ትምህርት ስትራቴጂና **መመሪያዎች፣** | | | |

**ሰ) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡**





| ተቁ | የመመሪያው ዓይነት | አለ | የለም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቻርቶች (Charts) | | | |
| 2 | የቃላት ካርድ (Word Card) | | | |
| 3 | ፍላሽ ካርድ (Flash card) | | | |
| 4 | ሻሽ ቦርድ (Shash board) | | | |
| 5 | ሥዕሎች (Picture cards) | | | |
| 6 | Black-board ruler | | | |
| 7 | Metre | | | |
| 8 | Balance | | | |
| 9 | Geometrical surfaces and solid samples | | | |
| 10 | **የግድግዳ ካርታዎች** | | | |
| | የዓለም ካርታ | | | |
| | የአፍሪካ ካርታ | | | |
| | የኢትዮጵያ ካርታ | | | |
| | የክልል ካርታ | | | |
| | የወረዳ ካርታ | | | |
| | የቀበሌ | | | |

2. **ለተንቀሳቀሽ አ/መ/ትምህርት ጣቢያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፤**

ጥቁር ሠሌዳ፣ አለ የለም

የተማሪዎች መቀመጫ አለ የለም

መልስዎ **"አለ"** የሚለው ከሆነ የመቀመጫውን ዓይነት ያመልከቱ /ለምሣሌ፤

ጀባ፣

ፕላስቲክ ምንጣፍ

በርጩማ

ፕላስቲክ ኩርሲ

ሌላ ______________________________

የተማሪ አስደግፎ መፃፊያ አለ የለም

የጽህፈት መሣሪያዎች፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ ሰነዶች፣ ወዘተ፡ ለማጓጓዝና

በጥንቃቄ ለማኖር የሚያስችል ቁልፍ ያላው / የተሰራለት የሚቆለፍ ሣጥን ወይም ሻንጣ፣

አለ የለም

## III. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አመቻቾችን በተመለከተ፡

### 1. የአመቻቾች ብዛት በትምህርት ደረጃ፡

| የትምህርት ደረጃ | ወንድ | ሴት | ድምር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ከ8ኛ ክፍል በታች | | | | |
| 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ | | | | |
| 9ኛ ክፍል ያጠናቀቀ | | | | |
| 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ | | | | |
| ሠርተፊኬት | | | | |
| ከሠርተፊኬት በላይ | | | | |

### 2. የአመቻቾች የቅድመ ሥራ ሥልጠና፡

የቅድመ ሥራ ሥልጠና ያገኙ አመቻቾች ብዛት





ወንድ ______ ሴት ______ ድምር _________

ሥልጠናው የወሰደው ጊዜ፤

| ሥልጠናው የወሰደው ጊዜ | ተሳታፊ አመቻቾች ብዛት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | |
| ከ30 ቀናት በታች የሰለጠኑ | | | | |
| ከ30 እስከ 45 ቀናት የሰለጠኑ | | | | |
| ከ45 ቀናት በላይ የሰለጠኑ | | | | |

3. **የአመቻቾች የማስተማር ብቃት፡**

| የሚጠበቁ ተግባራት | ያለበት ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በጣም ጥሩ | ጥሩ | አጥጋቢ | ዝቅተኛ |
| የክፍል አመራር /አያያዝ/፣ | | | | |
| የተከታታይ ግምገማና ምዘና ዘዴ አተገባበር፣ | | | | |
| የተማሪና የትምህርት ውጤት መረጃ አያያዝ፣ | | | | |
| የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት /ዓመታዊ፣ ወርኃዊ፣ ሣምንታዊና ዕለታዊ የትምህርት መርሐ ግብር/፣ | | | | |
| የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም፣ | | | | |
| ተስማሚ የትምህርት አቀራረብ ዘዴ አመራረጥ፣ | | | | |
| በልዩ ትምህርት ፍላጎት ዙሪያ ያለው ግንዛቤ፤ | | | | |
| ለሴት ተማሪዎች የሚደረግ የተለየ እገዛ፣ | | | | |
| ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች የመምረጥ፣ የማዘጋጀትና የመተግበር ችሎታ፣ | | | | |

4. **ሌላ**

አመቻቹ ትምህርት የሚሰጥበት አካባቢ ነዋሪ የሆነ ነው?

አዎ ☐ አይደለም ☐

አመቻቹ በአካባቢው ቋንቋ መናገር፣ መፃፍና ማንበብ ይችላል?

መናገር ይችላል ማንበብ ይችላል





መፃፍ ይችላል ሁሉንም ይችላል

## IV. የትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት፤

- ዓመታዊ የትምህርት ካሌንደር፤ አላቸው የላቸውም

መልስዎ **"አላቸው"** የሚል ከሆነ

- የዓመቱ ትምህርት መጀመሪያ ጊዜ ይገለጽ ______________
- የዓመቱ ትምህርት ማጠናቀቂያ ጊዜ ይገለጽ ______________
- የትምህርት ካላንደሩን ሥራ ላይ ለማዋል ህብረተሰቡ፡

  ተስማምቶባታል አለተስማማበትም

- የባከኑ የትምህርት ቀናት ፡ ተካክሰዋል አልተካካሱም

**እንደ ሙዚቃ፣ ሥዕልና የሰውነት ማጎልመሻ ያሉ የትምህርት ዓይነቶች**

- የተለያ ክፍለ ጊዜ ሳይያዝላቸው በዋናነት ከሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች ጋር ተቀናጅተው ይሰጣሉ፡፡
- የተለየ ክፍል ጊዜ ተይዞላቸው ይሰጣሉ
- አይሰጡም

## V. ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች

1. **የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል አገልግሎት፡**

ተማሪዎቹ የትምህርት ማበልፀጊያ አገልግሎት፡ ያገኛሉ አያገኙም

መልስዎ **"ያገኛሉ"** የሚል ከሆነ ከየት?

## VI. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም የየደረጃው ትምህርት ማጠናቀቂያ ምዘና፣ የትምህርት ማስረጃና የተማሪዎች ሽግግር

### 1. የየደረጃው ትምህርት ማጠናቀቂያ ምዘና፡

- ተከታታይ የትምህርት ምዘና (continuous Assessment) ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሆኗል?

  አዎ ☐ አይደለም ☐

- ተማሪዎች ከአንዱ ትምህርት ደረጃ ወደሚቀጥለው የሚሸጋገሩት በተከታታይ ምዘናዎች ተገምግመው ነው? አዎ አይደለም

### 2. የየደረጃውን ትምህርት ላጠናቀቁ ተማሪዎች የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች፡

- በየዓመቱ መጨረሻ የአንድ ክፍል (ደረጃ) ትምህርት መጠናቀቁን የሚገለጽ የውጤት መግለጫ ሠርተፊኬት (ሪፖርት ካርድ) ለተማሪ ይሰጣል

  አዎ ☐ አይደለም ☐

- ከክፍል ወደ ክፍል ዝውውርና የትምህርት ቤት ቅያሬ በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ስታንዳርድና በአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር ትምህርት አፈፃፀም መመሪያ መሠረት ነውን ?

  አዎ ☐ አይደለም ☐

- በአንደኛው ፕሮግራም የተጀመረውን ትምህርት በሌላኛው ፕሮግራም /መደበኛ፣ ቋሚና ተንቀሳቃሽ አመራጭ መሠረታዊ ትምህርት/ ለመቀጠል የሚቀርበው የዝውውር ጥያቄ በመመሪያው መሠረት ይፈፀማል

  አዎ ☐ አይደለም ☐





## VII. የሕብረተሰብ ተሳትፎ ማረጋገጥን በተመለከተ፡

| የተሳትፎው ዓይነት | የአፈፃፀም ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በ/ጥሩ | ጥሩ | አጥጋቢ | ዝቅተኛ |
| የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ለመማርማስተማሩ ሂደት ምቹ ማድረግ | | | | |
| የትምህርት መስጫ ቦታና ጊዜ በመወሰን መሳተፍ | | | | |
| የትምህርት ስራ በአግባቡ መካሄዱንና ተማሪዎችም በሚገባ መማራቸውን በመከታተልና በመቆጣጠር | | | | |
| ለችግረኛና ወላጅ አልባ ህፃናት ድጋፍና እንክባኬ በማድረግ | | | | |
| እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን /ወንድና ሴት/ ወደ ትምህርት ቤት በማምጣት | | | | |
| አመቻቾችን በመምረጥ | | | | |
| ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ አገልግሎት የሚውሉ የትምህርት ቁሳቁሶችን በማሟላት | | | | |
| የተንቀሳቃሽ ትምህርት መስጫ ጣቢያ የሚገኝበትን ቦታና የቆይታ ጊዜ የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎችን ለወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት በመስጠት | | | | |
| በጣቢያው የትምህርት እቅድና የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ መሳተፍ | | | | |
| ለአመቻቾች መጠለያ በማዘጋጀት | | | | |
| የስራ ሃላፊነታቸውን በሚገባ ለሚወጡ ትጉህና ታታሪ አመቻቾች ማበረታቻ በመስጠት | | | | |
| በቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ግንባታ የጉልበትና የቁሳቁስ አስተዋጽኦ ማድረግ | | | | |
| ትምህርት ቤቶችን በሚወክላቸው አባላት አማካኝነት የትምህርት መስጫ ጣቢያውን በበላይነት መምራትና ማስተዳደር ፤ | | | | |
| ለትምህርት እንቅፋት የሆኑ ወጎችና ልማዶችን ተመካክሮ በማስቀረት፣ | | | | |